www.abyssinialaw.com

# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

**ለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ**

**የስልጠና ማኑዋል**

# የተሻሻለው የውል ህግ ሞጁል

**በፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያወች ስልጠና ማእከል የተዘጋጀ**

# መግቢያ

ሰዎች በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሲኖሩ ያላቸውን ይሰጣሉ ያሌላቸውን ይቀበላሉ፡፡ የሚበሉት፣ የሚጠጡት፣ የሚጓጓዙበት፣ የሚያስደስታቸውን ነገር የሚያገኙበት ሁኔታ ሁሉ ምንጩ ከሰዎች ጋር የሚኖራቸው የሸቀጥ ልውውጥ ነው፡፡ ታዲያ ሂደቱ አስተማማኝ እንዲሆን፣ በንብረቶቻቸው ላይ ያሏቸው መብቶች ዋስትና እንዲያገኙ የልውውጡን ሥርዓት የሚገዛ ህግ ያስፈልጋልን፡፡ ይህ ሲሆን ልወውጡ እርካታን ያስገኛል፤ በፍርሃት ወይም በሥጋት የተነሳ የልውውጡ አድማስ ያልጠበበት ግንኙነት ይፈጠራል፤ ማንም ሰው በቀላሉ ወደ ገበያ ይገባል፣ ይወጣል፤ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የንግድ ልውውጥ ይመሰረታል ማለት ነው፡፡ በዚህ የተነሳም ልማት ይፋጠናል፣ ህብረተሰቡም ያተርፋል፡፡ የዚህ ሁሉ መሠረት በአግባቡ የተደራጀ በልውውጥ ሂደት የሚኖሩ ግንኙነቶች የሚመራ የውል ህግ መኖሩ ነው፡፡

ስለሆነም ህጉ ይህን ውጤት እንዲያስገኝ ታልሞ የተሠራ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ትርጉም ባለው መንገድ ለማስፈፀምም መሠረቱ የቆመበትን የኢኮኖሚ አመክንዮት መረዳት ግድ ይላል፡፡ እርግጥ የውል ህግ የኢኮኖሚ አመክንዮ ውጤት ብቻ ነው ማለት አይደለም፡፡ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሞራላዊ እሴቶች ማራመጃ መሳሪያም ጭምር በመሆኑ የፅንሰ ሃሳቦቹን መነሻ ምን እንደሆን ማወቅ፤ ተደራርበው በተገኙ ጊዜም በየጉዳዩ ልዩ ሁኔታ የትኛው የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ መለየትን ይጠይቃል፡፡

በዚህ እሳቤ መነሻነት መጠነኛ ሃሳብ ለማግኘት እንዲረዳ የዚህ ማኑዋል ሁለተኛ ምእራፍ የውል ህግ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ሚና ለማሳየት ይሞክራል፡፡ አልፎ አልፎም በየቦታው ይኸው ሃሳብ ይንፀባረቃል፡፡ በቂ አይደለም፡፡ ጊዜ ወስዶ መስራት ይጠይቃል፡፡ የሆነ ሆኖ ግን የዚህ ምእራፍ ዋና አላማ ህጉ በህግ ንድፈ ሃሳብ እና አመክንዮት ብቻ የታጠረ አለመሆኑን ለማሳየት ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ያሉት ምዕራፎች በውል ህግ ሊነሱ የሚገባቸውን ዝርዝር ነገሮች በተሟላ መንገድ የያዙ ሳይሆን ብዙ ጊዜ በፍርድ ቤት የሚያጋጥሙትን ውይይት ያስፈልጋቸዋል የተባሉትን ርዕሶች ብቻ የያዘ ነው፡፡ በመልመጃዎች የተደገፈ ስለሆነ ሠልጣኞችን በሚገባው ደረጃ በማወያየት ወደ ስራ ሲሰማሩ በክህሎት ዝግጁ ያደርጋቸዋል የሚል እምነት አለን፡፡

በምዕራፍ ሦስት ስለውል ማፍረስ እና መሠረዝ፣ ውል እንዲፈርስ ለመጠየቅ መብት ስላለው ወገኖች እናያለን፡፡ በምዕራፍ አራት ደግሞ ስለውል አለመፈፀም ደንብ እና ስለውጤቱ እንነጋገራለን፡፡

በመጨረሻው ምዕራፍ ስለዋስትናዎች በአጠቃላይ እናያለን፤ የንብረት ዋስትናን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በተዘጋጀው የሥልጠና ማኑዋል ብዙ ጊዜ የማናስተውላቸው ድንጋጌዎች በየመልኩ ተዘጋጅተው የቀረቡበት ስለሆነ በዚህ የሥልጠና ማኑዋልም ባሉበት ሁኔታ እንዲካተቱ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## የውል ህግ መሠረታዊ ሃሳቦች

**አጠቃላይ ዓላማዎች**

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ የውል ህግ

- በሰዎች ግንኙነት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ይለያሉ
- የውል ህግ መሠረታዊ ፅሳቤዎችን ይረዳሉ

**ዝርዝር ዓላማዎች**

ሠልጣኞች ሥልጠናውን ሲጨርሱ የውል ህግ

- በሰዎች ግንኙነት መሃል ሊኖር ኃላፊነትን የሚደለድል መሆኑን ይረዳሉ
- አስተተማማኝኝ የወደፊት ግንኙነት መመሥረቻ መሳሪያነቱን ይገነዘባሉ
- ከኢኮኖሚ ሥልጠት ጋር ያለውን ግንኙነት ይረዳሉ
- ኪሳራን የማሸጋገር ዓላማ ያለው መሆኑን ይረዳሉ

## 2.1 የውል ህግ ተግባራት

### 2.1.1 የተዋዋዮችን ግንኙነት ማደራጀት (the coordination role)

ውል ማለት ንብረታቸውን የሚመለከቱ ተነፃፃሪ ግዴታዎችን ለማቋቋም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው የፍ.ብ.ህ.ቁ 1675 (1) ። ስምምነቱ የሚቆመው በነፃ ፈቃድ ላይ ነው። ይህ በሁሉም የህግ ስርዓቶች ያለ መሰረታዊ ሀሳብ ነው። በነፃ ፈቃድ የመሠረቱት ውል ሊከበርን ይገባል ብለው ባሰቡት መንገድ የሚፈልጉትን ቁምነገር እንዲያካትት አድርገው ይቀርጹታል። ይህም በተዋዋዮች መካከል ፅርካታን ያመጣል ተብሎ ይታሰባል።

ይሁንና የሰው ልጅ ውሱንነት (Limited rationality) ያለበት በመሆኑ የህይወት አጋጣሚዎች በስምምነታቸው ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተፅዕኖ አስቀድሞ ለማየት ከመቸገር ክፍተቶቸ

ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ውሉ ምሉዕነት ይጎድለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ማን ምን ማድረግ አለበት የሚለው ጉዳይ በተዋዋዮች መካከል ውዝግብ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በመተማመን ላይ የሚመሠረቱ ግንኙነቶችን ይጎዳል፡፡ ዳፋውም ተከታታይ የሆኑ የንግድ ትስስሮችን ያበላሻል፡፡ የልውውጥ ሂደትን ይጎዳል ማለት ነው፡፡ የውል ህግ መኖር አስፈላጊነት የሚመጣው እዚህ ላይ ነው፡፡ ተዋዋዮች ሳይገልጿቸው ያለፏቸው ነገር ግን ግንኙነታቸውን የሚጎዱ ነገሮች ሲኖሩ ህጉ በነርሱ ዝምታ ውስጥ የታለፈውን ጉዳይ ለመሸፈን ይመጣል “Default rules” ይባላሉ፡፡ ከተዋዋዮቹ ውስጥ ማን ምን እንደሚጠበቅበት በመግለጽ እያንዳንዳቸው በውሉ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ያጠራል፣ ነገሩ እንዴት መፈጸም እንዳለበት በዝርዝር በማስፈር አንዱ ወገን በውሉ ዝምታ ምክንያት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም እንዳያገኝ ይገታል፡፡ በተዋዋዮች መካከል የሚኖረውን ትርምስ ያስቀራል፡፡ ወንድማማችነት ይፈጠራል፡፡ ግንኙነታቸውንም መልክ በማስያዝ ልውውጦችን ቀና ያደርጋል፡፡ በሌላ አገላለጽ ለጋራ ጥቅም ኃላፊነትን በመደልደል በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት ያደራጃል (ያቀናጃል) ማለት ነው፡፡ ደግምም “Default rules”ን በመተማመን በያንዳንዱ የግንኙነቶቻቸው ሂደት ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እየተጨነቁ ሳያስቡ ግንኙነቶቻቸውን እንዲመሩ ይረዳል፡፡

## 2.1.2 አፈፃፀማቸው ጊዜ የሚጠይቅ ስምምነቶችን አስተማማኝ ማድረግ

ውሎች በአብዛኛው የሚፈፀሙት እጅ በእጅ (on the spot) በሚደረግ ልውውጥ ሲሆን የትኛውም ወገን ከስምምነቱ አገኛለሁ የሚለውን ጥቅም ስምምነቱ እንደተፈፀመ ያገኛል፡፡ ውሉ የሚመሰረተውም የሚፈፀመውም እዚያው ላይ በመሆኑ በለውጡ የሚያገኘው የሚፈልገውን እንደሆነ ይታሰባል፡፡ በየዕለቱ የሚታዩትን ልውውጦች ያህል ውዝግብ አለመኖሩ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡

ይሁንና በገሃዱ ዓለም ስምምነቶች ሁሉ እጅ በእጅ የሚከናወኑ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ አፈፃፀማቸው በጊዜ ሂደት የሚከናወን ስምምነቶችም አሉ፡፡ በውሉ አመሰራረትና በአፈጻጸሙ መሃል የጊዜ ክፍተት ሲኖር ተዋዋዮች እንደስምምነቱ ቃላቸውን የሚያከብሩ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስቸግራል፡፡ መተማመን ይጎድለናል፡፡ እናም እንዲህ ያሉ ስምምነቶች ውስጥ ለመግባት እናመነታለን፡፡ ብንገባም እንኳ ሊደርስ የሚችለውን ኪሳራ በማሰብ ስምምነቶቻችንን ከምናውቃቸው እና ከምንተማመንባቸው ሰዎች ጋር ብቻ እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ የልውውጡ አድማስ ይጠባል ማለት ነው፡፡ ይህ የሸቀጦችን ዋጋ ያንራል፣ በመደበኛ ሂደት የሚኖረውን የልውውጥ ወጪ ከፍ

ያደርጋል፡፡ የውል ህግ መኖር ይህ እንዳይሆን ይጠብቃል፡፡ ሰው በቃሉ ይታሰራል *(pacta sur servanda)* [የፍ.ብ.ህ.ቁ 1731(1)] የሚለው ጽንሰ ሃሳብ መሠረትም በፈቃድ የገቡትን ግዴታ ተዋዋዮች እንዲያከብሩ በማድረግ የሞራል ግዴታ ይጥልባቸዋል፡፡ አንዱ ተዋዋይ በሌላው ላይ ያደረሰውን ጉዳት እንዲክስ [የፍ.ብ.ህ.ቁ. 1790 እና 1791[ በመደንገግም ጉዳት ሊደርስበት የሚችል ተዋዋይ ቢኖር እንዳይሰጋ ያደርጋል፡፡ ጥበቃው በውሎች ላይ ሊኖር የሚችለውን መተማመን ይጨምራል፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ማንም ሰው ያለውን ለሌላው አሳልፎ ይሰጣል ብሎ ማሰብ ይከብዳል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ጥቅሞቻችን በሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ ይሆኑና ልናገኝ የምንፈልገው ነገር ከአንድ ክስተት በፊት ወይ በኃላ የመምጣቱ ነገር ውል ለማድረግ በሚኖረን ውሳኔ ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ በምሳሌ ለመግለጽ ያህል አንድ አደጋ ከተከሰተ በኃላ ንብረቱ የወደመበት ሰው አረቦን (premium) ልክፈልህ እና በንብረቴ ላይ የደረውን ጉዳት ጠግንልኝ በማለት አንድን የኢንሹራንስ ኩባንያ ቢጠይቅ ኩባንያው ፈቃደኛ አይሆንም፤ በተመሳሳይ ሁኔታም ጉዳት ከመድረሱ በፊት የንብረቱ ባለቤት የሆነ ሰው አረቦን (premium) የመክፈል ዝንባሌ አይኖረውም ወይም አነስተኛ ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ልውውጥ በእጅ ለእጅ ገበያ ውስጥ ማግኘት አይቻልም፡፡ አስቀድሞ የሚደረጉ የቃል መግባቶችን የሚጠይቁ ናቸው:: ታዲያ ህጉ ይህን እና መሰል ስምምነቶች እንዴት መመስረትና መመራት እንዳለባቸው ሥርዓት በማበጀት ልውውጡን ቀና ያደርጋል፡፡

ስለሆነም በአንድ ውል መመስረት እና በአፈፃፀሙ መሃል ያለው የጊዜ መስፋት ስለ አፈፃፀሙ ያለንን ዕምነት ሳይሸረሽር፣ ወደፊት ሊኖረን የሚገባውን ግንኙነትም ከወዲሁ ለማዘጋጀት የሚያስችል ማዕቀፍ በማዘጋጀት ልውውጦችን ቀና እና አስተማማኝ ያደርጋል ማለት ይቻላል፡፡

### 2.1.3 ስምምነቶች የሚኖራቸውን ጉድለት መሙላት

በህግ ክልከላ የተደረገበት ካልሆነ በቀር ውል ያቋቋሟቸው ወገኖች ስምምነታቸውን በፈቀዱት መንገድ ለመፈጸም ቃል የሚገቡበት ሰነድ ነው፡፡ በዚህ ስምምነት ተዋዋዮች ምን ሰጥተው ምን መቀበል እንደለባቸው ያውቃሉ፣ መቼ እና እንዴት ማከናወን እንዳለባቸውም በዝርዝር በመግለጽ ይስማማሉ፡፡ ሆኖም ስምምነታቸው በሚከሉት ምክንያቶች ምሉዕ ላይሆን ይችላል

*ሀ. የተዋዋዮች ውሱንነት*

ተዋዋዮች በአንድ ጉዳይ ሊደራደሩ ይችላሉ። ሲስማሙ ውዝግብ ቢነሳ እንኳ ማንም ሰው ሊረዳቸው በሚችል መንገድ የተስማሙባቸውን ነጥቦች በግልጽ እና በዝርዝር ለመቅረጽ ይጥራሉ። ነገር ግን ሰዎች ውሱን አዕምሮ ያለቸው በመሆኑ በጊዜ ሂደት የህይወት ውጣ ውረድ (externalities) በግንኙነታቸው ውስጥ ሊፈጥር የሚችለውን ተፅዕኖ አስተማማኝ በሆነ መንገድ ሊያውቁ አይችሉም ወይም ለማወቅ ይቸገራሉ። ስለሆነም በግንኙነታቸው ሚዛን ላይ ጊዜ የሚፈጥረውን ተፅዕኖ አለማወቃቸው ውሉ ምሉዕነት እንዲጎድለው ምክንያት ይሆናል።

*ለ. ዝርዝር መሆን የሚጠይቀው ዋጋ*

ሰዎች ሊኖራቸው የሚችለውን የውል ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት እስከ ፍፃሜው ድረስ አስቀድሞ በማየት የተሳካላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ዋና ከሚባሉ ጉዳዮች አልፈው የታዩዋቸውን ጥቃቅን ዝርዝሮች ሁሉ መፃፍና መስማማት ላይፈልጉ ይችላሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ጥቃቅን ዝርዝር ላይ የሚደረገው አለመስማማት ዋና እና መሰረታዊ ነው የተባለውን ጉዳይ ሊያደፈርስ ይችላል። በሁለተኛ ደረጃም በእያንዳንዱ ጥቃቅን ዝርዝር ላይ ለመነጋገር መጨነቅ የራሱን ጊዜ የሚወስድና ወጪንም የሚጠይቅ ሂደት በመሆኑ ነው። ስለሆነም ተዋዋዮች በ "default rules" በመተማመን ዋና ነገሮች ላይ ብቻ በማተኮር ዝርዝሩን ሊተውት ይችላሉ።

*ሐ. ውል በትክክል ሊፈጸም የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻል*

በብዙ አጋጣሚዎች ስምምነቶች እንደተዋዋዮች ፈቃድ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ ይቻል ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ግን እርግጠኛ ለመሆን አይቻልም:: እጅ በእጅ በሚደረግ ልውውጥ ውስጥ እንኳ ይህን መተማመን ለማግኘት ያስቸግራል:: አንድን ምርት በግዢ የተቀበለ ሰው የተረከበው ምርት ጥራት፣ አሰራር በውሉ ላይ በሰፈረው ዓይነት ስለመሆኑ በርክክቡ ጊዜ ለመረዳት ይከብደው ይሆናል። ተፈላጊው ማሽን ለተፈለገበት ዓለማ የተገባ መሆኑን ለማወቅ በዕጃችን ከገባ በኂላ ሥራ ላይ ስናውለው ችግር መፍጠሩን እስክናይ የተረከብነው በስምምነቱ መሰረት እንደሆነ ልናስብ እንችላለን ። በተመሳሳይ ሁኔታም የተረከብነው የስንዴ ዱቄት ጊዜው ያለፈበት የተበላሸ መሆኑን የምንረዳው

በርክክቡ ጊዜ ሳይሆን ከርክክቡ በኃላ ስናቦከውም ሆነ ስንጋግረው ከደንበኛው ዱቄት የምንጠብቀውን ውጤት ያልሰጠን መሆኑን ስናይ ነው እንደውሉ ያልተፈፀመልን መሆኑን የምንረዳው፡፡

ታዲያ ውሉ በሚመሰረትበት ጊዜ እንዲህ ያሉትን ሁኔታዎች ቀድመን ለማወቅ እንቸገራለን፡፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በነገሩ ላይ ያለን ዕውቀት ዝቅተኛ መሆን ወይም በጊዜው ዝርዝር ነገሮችን ማረጋገጥ ውስብስብነት ያለው፣ ጊዜና ወጪን የሚጠይቅ መሆኑ በዝርዝሩ ላይ በርግጠኝነት ለመደራደር እንዳንችል ያደርገናል፡፡ ስለዚህም መሠረታዊ በሆኑት ላይ ብቻ በማተኮር ቀሪዎችን ዝርዝሮች እናልፋለን፡፡ አንዱ ተዋዋይ አውቆት ቢሆን እንኳ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን የዕውቀት ውሱንነት በመገመት በዕኩይ መንፈስ ነገሩ ሳይነሳ እንዲያልፍ መፈለግም ሌላው ለዝርዝር ነገሮች መታለፍ አንድ ምክንያት ሊሆን የሚችል ነው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ አንድ ውል በየትኛውም ምክንያት ቢሆን ምሉዕነት ላይኖረው ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ህጉ ተዋዋዮች በውሉ ጊዜ የነበራቸውን ሀሳብ ምን እንደነበር ለማወቅ ዳኛው ጥረት ማድረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይህን ለማድረግ የተዋዋዮች ግንኙነት ምን እንደነበር፣ በውሉ አፈፃፀም ሂደት የነበራቸው ሚና መለየት፣ ፍትህ እና የኢኮኖሚ ሥልጠት እንዲሁም ሌሎችንም ምክንያታዊ የሆኑት ነገሮችን የሚጠይቁትን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት መመርመር የሚጠይቅ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የሆኖ ሆኖ ህጉ የአተረጓጎም ሥርዓቶችን በማበጀት ክፍተቱን (የውሉን ጉድለት) ይሞላል፡፡

## 2.2 የውል ህግ አወቃቀር (the design of contract law)

### 2.2.1 የኢኮኖሚ ስልጠትን መፍጠር

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ውል ንብረቶቻቸውን የተመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም፣ ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት የተነሳ ሰዎች በመካከላቸው የሚመሰረቱት ስምምነት ነው ብለናል፡፡ የግንኙነታቸው መሰረት ንብረት ነው፡፡ ወጪን ያንራል፣ በገበያ ላይ ያለን መተማመን ያጎድላልና ሰዎች ንብረቶቻቸው ከአንዱ ወደ ሌላው ሲያሳልፉ የልውውጡ ፍሰት እንዲታጎል አይፈልጉም፡፡ ይህ የተዋዋዮች ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው ሕዝብ ፍላጎትም ጭምር ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ታዲያ የውል ህግ የገበያው ተሳታፊዎች ሊኖራቸው የሚገባው ጠባይ ምን መሆን፣ እንዴት መመራት እንዳለበት ደንብና ሥርዓት በማበጀት የልውውጡ ሂደት መተማመን ያለበት

ጊዜና ወጪን የሚቆጥብ የሰዎችን ዕርከታ የሚያስገኝ እንዲሆን ተደርጎ ይዋቀራል፡፡ ስለሆነም የውል ህግ በሰዎች መካከል ያለውን ቀና የሆነ የኢኮኖሚ ግንኙነት የሚገዛ መሳሪያ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡

ነገሩን ለማብራራት ያህል ስልጠት ከሰዎች ርካታ አንጻር ሊገለጽ ይችላል፡፡ አንድ መጽሀፍ የገዛ ሰው ለገዛው መጽሀፍ የከፈለው ዋጋ መጽሀፉ ለርሱ ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንጻር ሲታይ ጥሩ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አነስተኛ ዋጋ ሊሰጠው የሚችል ሌላ ሰው አለ ተብሎ አይታሰብም፣ ቢታሰብም ራሱን የቻለ የጊዜና የገንዘብ ወጪ ሳይጠይቅ የሚፈፀም አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መጽሀፉን የሸጠው ሰው በበኩሉ ስለመጽሀፍ ሽያጭ የተቀበለው ዋጋ ዕርካታን ይሰጠዋል በተመሳሳይ ዋጋ መጽሀፍን የሚገዛው ሰው ባለመኖሩ ከሽያጩ ደስታን አትርፏል፡፡ እንዲህ ሲሆን ሸቀጦች (resources) ከፍ ያለ ተጠቃሚነት ወደሚያገኙት ሰዎች ተሸጋግሯል ማለት ይቻላል፡፡ ስልጠት ማለትም ሀብቶችን ለሰዎች ከፍተኛ ዕርካታን በሚያስገኝ በዚህ ዓይነት መንገድ መጠቀም ማለት ነው፡፡ ህጉ ይህንን እንዲያበረታታ ተደርጎ የተቀረጸ ነው፡፡ ሰው በቃሉ ይታሰራል የሚለውን መርህም አንዱ የዚህ ማስፈጸሚያ መሳሪያ አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በአንፃሩ አንድን ሸቀጥ በማታለል ወይ በኃይል ያገኘ ሰው ቢኖር በዚህ መንገድ የተደረገው ልውውጥ የኢኮኖሚ ስልጠትን የሚያስገኝ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አንዱ ወገን መረጃን በሞኖፖል መያዝ ብቻ ሳይሆን መረጃን በማሳሳት ወይም ደግሞ ከተዋዋዮቹ ውስጥ የአንዱ የመደራደር አቅም በማይገባ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ መተማመንን በማጉደል የገበያ ውድቀትን የሚያስከትል በመሆኑ ነው፡፡ በግለሰብም ሆነ በህብረተሰብ ደረጃ ሁኔታውን ለመቆጣጠር ከፍ ያለ ወጪን ይጠይቃል፡፡ እናም የኢኮኖሚ ስልጠትን አይፈጥሩም፡፡ ህጉ ይህን አያበረታታም፡፡ መገደድ እና ማታለልን የማይደግፉ ህጎች የተቀረጹትም እንዲህ ያሉ የኢኮኖሚ ስልጠት የማይፈጥሩ ጠባያትና ሁኔታዎችን በመቆጠጠር ተፈላጊውን ስልጠት ለማስገኘት ሲባል ነው፡፡

ስለሆነም ህጉ ብቸኛው ባይሆንም አንድ የኢኮኖሚ ስልጠትን የሚያስገኝ መሳሪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል ማለት ነው፡፡

### 2.2.2 ኪሣራን ማሸጋገር

ሸቀጦች በጊዜ ሂደት የዋጋ ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ይህ ፍርሀትን ይፈጥራል፡፡ በዚህ የተነሳ ሰዎች በመጪው ጊዜ በሚኖረው የዋጋ ልዩነት ተጎጂ እንዳይሆኑ ከወዲሁ ስምምነት በማድረግ

የወደፊቱን ዋጋ ዛሬ ላይ ለማሰር ይገፋፋሉ፡፡ ሱራፌል በመጪው ሰኔ በብር 150 አንድ ኩንታል ስንዴ ሊያስረክበኝ ቃል ባይገባ ኖሮ ሰኔ ሲደርስ በብር 250 ለመግዛት እሱም ቢሆን ዋጋው ሲወርድ በወረደው በብር 50 ዋጋ ስንዴውን እንደቅደም ተከተላችን ለመግዛትና ለመሸጥ እንገደድ ነበር፡፡ ስምምነት ከተደረገበት ዋጋ አንፃር የወጣውን ወይም የወረደውን ዋጋ ልዩነት ስናይ የልዩነቱ መጠን በአንዳንችን ላይ ሊደርስ ይችል የነበረው በስምምነት አንዳችን በሌላችን ላይ ያስተላለፍነው ኪሳራ ነው፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ሰው በሚፈፅመው ውል ላይ ይህን አገላለጽ ቃል በቃል ላያገኘው ይችላል፡፡ ይሁንና የስምምነቱ ይዘት በጥልቀት ሲመረመር የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡

ታዲያ የተደረገውን ስምምነት የሚያስፈጽም የውል ህግ ባይኖር መጪውን ጊዜ ባየነው መጠን የሚደርሰውን ኪሳራ ለማስተላለፍ ባልተቻለን ነበር፡፡ አሁን ግን ተዋዋዩ በስምምነታችን መሰረት ስንዴውን ሊያቀርብልኝ ይገደዳል፤ በርክክቡ ጊዜ ባለው ዋጋ መሸጡ የበለጠ ሊያተርፈው ቢችል እንኳ የውሉን ግዴታ ከመፈጸም ሊሸሽ አይችልም፡፡ መሸሽ ቢችልም በርክክቡ ጊዜ ስንዴ ለመግዛት የምገደድበትን የኪሳራ ገንዘብ እንዲተካ ይገደዳል፡፡ ህጉ ይህን ዓይነት ግንኙነት እንዲያበረታታ ሆኖ የተቀረጸ ነው፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፡፡ ተዋዋዮች በስምምነታቸው ላይ ሳያሰፍሩት በቀሩ ጊዜ እንኳ ህጉ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት የሆነውን ችግር በተሻለ ሁኔታ ለመቆጣጠር ማን ይችል እንደነበር ከግምት ውስጥ በማስገባት ኪሳራን ያሸጋግራል (1802)፡፡

### 2.2.3 ማህባራዊ ፍትህ እና ርትዕን ማስፈን

እስከሁን ያነሳናቸው በአብዛኛው ከኢኮኖሚ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ውል በኢኮኖሚክ አመክንዮ ብቻ የተተበተበ ነው ማለት አይደለም፡፡ በውል ስምምነት ውስጥ እንዲኖር የሚፈለገውን ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር አጣጥሞ በማየትም ማህበራዊ ፍትህን የሚያሰፍን መሳሪያ ጭምር ተደርጎ ሊታይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የተዋዋዮች ስምምነት በነፃ ፈቃዳቸው ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል፡፡ አንዱ ወገን የሌላውን ፈቃድ ያገኘው በማስገደድ እንደሆነ እንዲህ ያለውን አጉል ጠባይ በመቆጣጠር አቅም የሌላቸውን ሰዎች ጥቅም ይጠብቃል፡፡ እናም ማኅበራዊ ፍትህን ያሰፍናል፡፡

ርትዓዊ ከመሆን አንጻርም አንዳንድ ግንኙነቶች የሚፈጥራቸውን ውጤቶች ከማኅበራዊው አኗኗር መለኪያ አንፃር እየታየ እንዲመዘን የሚፈቅድም ነው፡፡ ውጤቶቹ ፍትሀዊ መስለው በማይታዩ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች ዳኞች በርትዕ እንዲወስኑ ህጉ መብት የሚሰጣቸውም በዚህ መነሻ ነው፡፡ ህጉ ስለ

መጎዳት (unconscionability) እና ስለ ቅን ልቡና የሚያነሳውም ከዚሁ የርትዕ ጉዳይ ጋር የተያያዘ መሆኑን ማጤን ይገባል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ውል ማፍረስ/መሠረዝ

**የሥልጠናው ዓላማ**

ሠልጣኞች ከሥልጠናው መጠናቀቅ በኋላ የውል ማፍረስ ወይም መሠረዝ

- የኢኮኖሚክ አመክንዮቱን ይገነዘባሉ
- በሞራል ዕሴቶች ማራመጃ መሆኑን ይረዳሉ
- ከማህበራዊ ፍትህ ጋር ያለውን ግንኙነት ይረዳሉ
- ውል እንዲፈርስ ለመጠየቅ መብት ያለውን ወገን ይለያሉ
- የውል መፍረስ ውጠየትን ይገነዘባሉ

## 3.1 ውል የሚፈርስባቸው ሁኔታዎች

ህግ የሚጠይቀውን ሥርዓት ተከትሎ የተሰራ ውል በህግ ፊት ሊፈጸም የሚችል ነው፡፡ የተዋዋዮችን ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ ዕርካታን የሚያስገኝላቸው በመሆኑ እንደስምምነታቸው እንዲፈጸም የህጉ ፍላጎት ነው፡፡ ይሁንና ህጉ እንዲኖር የሚፈልገውን ወይም የሚጠይቀውን ሁኔታ የሚያሟላ ሳይሆን የገበያ ውድቀትን (market failure) ሊያመጣ የሚችል በመሆኑ ፍርስ ይሆናል ወይም እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡ ይህ አይነቱን ችግር ያስከትላሉ የሚባሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ናቸው፡፡

### 3.1.1 የፈቃድ ጉድለት

ውል ተነፃፃሪ ግዴታዎቻቸውን ተረድተው ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር በሚችሉ ሰዎች መካከል የተፈጸመ መሆን አለበት፡፡ አንዳንድ ሰዎች በዕድሜ ማነስ፣ በመጃጀት ወይም በአዕምሮ ጤንነት

ጉድለት ምክንያት ጥቅሞቻቸውን ተገቢ በሆነ መንገድ (rationally) ለማስጠበቅ ይችላሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ ይህ ህጉ የሚፈልገውን የጋራ ጥቅም የሚያስገኝ አይሆንም፡፡ እነኚህ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ለአደጋ የተጋለጡ ክፍሎች ስለሆኑ ህጉ ከለላ ይሰጣቸዋል፡፡ ስለሆነም የፈፀሙት ውል እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡ ይህን ማድረግ የሚችለውም በውሉ ተጎድቻለሁ የሚለው ወገን ብቻ ነው፡፡ ችሎታ ማጣቱን መከላከያ ሊያደርገው የፈለገ እንደሁ ውሉ በተደረገ ጊዜ ችሎታ እንደልነበረው ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ህጉ ማንኛውም ሰው ችሎታ አለው የሚል ግምት የሚወስድ በመሆኑ፡፡ ፍርስ ከመሆን ይልቅ ፈራሽ እንዲሆን የተደረገው ጠቃሚ የሆኑ የኢኮኖሚ ልውውጦች በየሰበቡ እንዳይታጎሉ ለማድረግ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም ህጉ መሰረታዊ ነው ብሎ የሚጠይቀው የነፃ ፈቃድ መኖር ለአንድ ውል ህልውና ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በነፃ ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ ስምምነት የጋራ የሆነ የኢኮኖሚ ጥቅምን (economic welfare) ዋጋ የሚቀንስ ነው፡፡ ስለሆነም ህጉ በነፃ ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ ስምምነትን አያበረታታም፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ክፍል እንደተገለጸውም አስተማማኝነትን የሚያጎድል፣ በግለሰብም ሆነ በህብረተሰብ ደረጃ የሚኖረውን ትርምስ ለመቆጣጠር ከፍ ያለ ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑ ተፈላጊውን ስልጠት አያስገኝም፡፡ ስለሆነም በፈቃዱ ጉድለት የተደረገውን ስምምነት እንዲፈርስለት ተጎጂው እንዲጠይቅ ህጉ እድል ይሰጠዋል፡፡

ለአንድ ተወዳዳሪ ገበያ (competitive market) መኖር አስፈላጊ ነው የሚባለው በቂ መረጃ ነው፡፡ በቂ መረጃ በሌለበት ሁኔታ የገበያው ተሳታፊዎች በሂደቱ ደስታን በሚያስገኝላቸው መንገድ የጋራ ጥቅማቸውን ያስከብራሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለሆነም ህጉ ቀና የሆነ የገበያ ውድድርን ለመጠበቅ ሲል በቂ መረጃ እንዳይኖር ዕንቅፋት የሚፈጥረውን አጋጣሚ አያበረታታም ስለዚህም በስህተት፣ በተንኮል እና በመጎዳት (unconscionability) የሚደረጉ ስምምነቶች ሲኖሩ ተዋዋዩ ውሉን እንዲያፈርስ ዕድል ይሰጣል፡፡

### 3.1.2. ከህግ ውጪ፣ ለሞራል ተቃራኒ መሆን እና ለውሉ አፃፃፍ የተደነገገውን ስርዓት ያልተከተለ መሆን

#### *ሀ. ከህግ ውጪ እና ለሞራል ተቃራኒ መሆን*

ማንኛውም ውል የህብረተሰቡን ጠቅላላ ጥቅም ለመጠበቅ በተዘጋጀው የህግ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲከናወን ይፈለጋል፡፡ ማኅበራዊ ህጉን (pubic law) ፣ ፖሊሲዎችን በሚቃረን መንገድ የተፈጸመ እንደሆነ ዕውቅና አያገኝም፡፡ ይህን መጣስ ተፈላጊውን ማህበራዊ ፍትህ አያስገኝም፡፡ ስለሆነም አይበረታታም፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፡፡ ህብረተሰቡን ከሚያስተሳስሩት ማህበራዊ ዕሴቶች ውስጥ አንዱ የኔ ናቸው፣ ሊጠበቁልኝ ይገባል የሚላቸውን የሞራል ዋጋዎች (moral values) መጠበቅ አንዱ የህጉ ዓለማም ነው፡፡ ስለሆነም እነኚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ያላስገባ ስምምነት ዕውቅና አይሰጠውም፡፡ ፍርስ እንደሆንም ይታሰባል፡፡

#### *ለ. ህጉ የሚጠይቀውን የአፃፃር ሥርዓት ተከትሎ የተሰራ አለመሆን*

ውሎች በተዋዋዮች ፈቃድ ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው፡፡ እንዴት እና በምን ዓይነት ሁኔታ መዋዋል እንደሚፈልጉ የሚወስነት እነሱው ናቸው፡፡ ህግ ጣልቃ አይገባም፡፡ ይሁንና የህብረተሰቡን ጠቅላላ ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር የተወሰኑ ገደቦች ይጣሉባቸዋል፡፡ አንዱ ህጉ ወሳኝና አስፈላጊ ናቸው በሚላቸው የውል ዓይነቶች ላይ ተዋዋዮች ሊከተሉ የሚገባውን የአፃፃፍ ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ የተለየ የአፃፃፍ ሥርዓት እነዲከተሉ በህግ የታዘዘ በሆነ ጊዜ የህጉ ቃል መከበር አለበት [1678 (3) (ሐ)] ፡፡ ይህ ማለት ህጉ በመርህ ደረጃ በፈቃድ ላይ የተመሰረተ ከመሆን አልፎ ፎርምን በመርህ ደረጃ አይጠይቅም ማለት ነው፡፡

ስምምነቶች አንድ ዓይነት የአፃፃፍ ሥርዓትን እንዲከተሉ የሚፈለግበት ምክንያት

1. ህጉ ዋና ናቸው በሚላቸው ጉዳዮች ላይ የተዋዋዮቹን ጥቅም አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመጠበቅ ታስቦ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ውል በጽሁፍ እንዲሆን መታዘዙ የውሉን ይዘት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ያቀላል፡፡ በዚህ ረገድ ሊኖር የሚችለውን ውዝግብም ይቀንሳል፡፡ በዚህ የተነሳም የሰዎችን የውል ግንኙነት ውጤታማ በሆነ መንገድ መምራት ይቻላል ማለት ነው፡፡ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አስተሳሰብም ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጊዜ፣ ወጪ እና ድካምን በመቀነስ ስልጠትን የሚፈጥር ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

2. ተዋዋዮች በችኮላ ቃል ከመግባታቸውና ይህም በነርሱ ላይ አስገዳጅ ከመሆኑ በፊት በጉዳዩ ላይ እንዲያስቡበት የአፍታ ጊዜ እንዲያገኙ (precautionary role) ማድረግ ነው፡፡

3. ደካማውን ተዋዋይ ወገን ለመጠበቅም ይረዳል፡፡ ሌለው ወገን ማስረጃው እንዲደርሰው በመጠየቅ የመደራደር አቅም የሌለውን ተዋዋይ ጥቅም ያስጠብቃል (protective function)፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ህግ ላይ አሠሪው ለሠራተኛው መቀጠሩን በጽሁፍ እንዲያሳውቀው እንደሚያዘው ማለት ነው፡፡ ታዲያ በነኚህ መሰረቶች ላይ የቆመውን ዓለማ ለማሳካት ውሉ ውጤት እንዲኖረው ከመደረጉ በፊት የተጠየቀውን ሥርዓት ማሟለቱን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡ ከተዋዋዮች እንዲነሳ ሳይጠበቅ ፍርድ ቤቱ ሊያነሳው የሚችለው ጉዳይ ነው፡፡ የህጉን ዓላማ ለማስፈፀም ከፍርድ ቤቶች የተሸለ ዕድል ያለው የለም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ ንቁ መሆን ይገባቸዋል፡፡

## 3.2 ውል እንዲፈርስ ለመጠየቅ መብት ስላለው ሰው፣ ስለሚጠየቅበት ጊዜ እና ስለውል መፍረስ ውጤት

### 3.2.1 ውል እንዲፈርስ ለመጠየቅ መብት ስላለው ሰው እና ስለሚጠየቅበት ጊዜ

ለአንድ ውል ውጤት ማግኘት የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች የተሟሉ እንደሆነ ይፈፀማሉ፡፡ የተጓደሉ እንደሆነ ግን ውሉ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡ ጥያቄውን ለማቅረብ የሚችለውም በፈቃዱ ጉድለት ወይም በችሎታው ማጣት ሰበብ በውሉ የተጎዳው ወገን ብቻ ነው፡፡ ሌላ ሰው ጥቅም ኖሮት ቢሆን እንኳ ለመጠየቅ አይፈቀድም፡፡ ውሉ ከህግ ውጪ ነው፣ ለህሊና ይቃረናል ወይም የተደነገገውን የአፃፃፍ ሥርዓት አልተከተለም በሚል ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ሥልጣን የተሰጠው ግን ለተዋዋዮችና በጉዳዩ ላይ ጥቅም አለኝ ለሚል ማንኛውም ሰው ነው፡፡ ይህ ልዩነት የኗለኞቹ ምክንያቶች ጉዳቱ ከተዋዋዮች ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትም በላይ ጠቅላላውን ህዝብ የበለጠ የሚጎዱ ቀውስን የሚፈጥሩ ናቸው በሚል ትኩረት የተደረገባቸው መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

ከዚህ በተረፈ ጥያቄዎቹ የሚቀርቡበት ሁኔታ በጊዜ የተገደበ ስለመሆኑ ከፍ.ብ.ህ.ቁ.1810 (2) መረዳት ይቻላል፡፡ ውል የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት አመት ውስጥ ውል

እንዲፈርስ መጠየቅ አለበት፡፡ ውል የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ማለቱ ውሉ የማይረጋበት ምክንያት የሚቀርባቸውን እንደችሎታ ማጣት፣ አቅመ-አዳም አለመድረስ ወይም መገደድ ያሉትን አጋጣሚዎች ለመግለጽ የታለመ ነው፡፡ ሌላው የጊዜ ገደብ የተቀመጠው በጉዳት ምክንያት unconscionable contracts የተደረጉ እና አካለ መጠን ያደረሰ ሰው ያደረጓቸውን ውሎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር በሁለት ዓመት ውስጥ እንዲፈርሱ ካልተጠየቁ ይፀናሉ፡፡

### 3.2.2 የውል መፍረስ ውጤት

አንድ ውል የማይረጋ በመሆኑ ምክንያት እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ በተቻለ መጠን ተዋዋዮች ወደነበሩበት ቦታ እንደመለሱ ማድረግ ይገባል፡፡ ውሉ የፀና ነው በሚል ዕምነት ውሉን በመፈፀም ረገድ የተደረጉ ስራዎች ካሉ ቀሪ ይሆናሉ፡፡ ውጤት ያሌላቸው ወይም የማያስገኙ ይሆናሉ፡፡ ይህ ማለት ስለውሉ አፈፃፀም የተደረጉትን አንዱ ለሌላው መመለስ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

ይህ የውል ማፍረስ ውጤት አንዱ ገጽታ ሲሆን ሌላው ደግሞ ተዋዋዮችን በተለያየ ምክንያት እነበሩበት ቦታ መመለስ የማይቻል፣ አስቸጋሪ ወይም ከፍ ያለ መሰናከል የሚያመጣ ሲሆን ህጉ የሚያስቀምጠው አማራጭ ነው፡፡ ስለውሉ አፈጻጸም የተሰሩ ሥራዎች ሁሉ እንደረጉ እንዲቀሩ ያዛል፡፡

ሁልጊዜም ማለት በሚቻል ደረጃ ውል ከፈረሰ በኋላ የመጀመሪያውን አማራጭ በመጠቀም ተዋዋዮች ወደነበሩበት እንዲመለሱ በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥ ስለመሆኑ በርካታ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቶች ሁለተኛውን አማራጭ ሲጠቀሙ አይታይም፡፡ መመላለስ የሚቻልበት ሁኔታ ሁልጊዜም ስላለ ነው ብሎ መደምደም ያስቸግራል፡፡ በቅርብ ጊዜያት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በነ ወ/ሮ ጎርፌ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ በየፍርድ ቤቱ የሚቀርቡ ጉዳዮች መብዛት ይህንን ክፍተት ለመጠቀም ከመሻት የሚነሱ ናቸው ብሎ በድፍረት ለመናገር ብዙ የሚያሳቅቅ አይደለም፡፡

## የውል መፍረስ/መሠረዝ ላይ ለማወያያነት የቀረቡ መልመጃዎች

1. የማይንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭን በተመለከተ ውሉ ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ወይም በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ፊት መሆን አለበት በማለት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ላይ ተገልጿል፡፡ ይህን አለማሟላት ውሉን ፍርስ ያደርገዋል? ወይስ ህጉ በወጣ ጊዜ እንዲህ ያሉትን ምዝገባ የማያከናውኑ ተቋማት ባልነበሩበት ጊዜ ስለሆነ በጊዜው የነበሩትን ውሎች ሁሉ ፍርስ የማድረግ ዓላማ ይዞ አልተነሳም፡፡ ይልቁንም ሕብረተሰቡ ስለደህንነቱ ውሎቹን በሚመለከተው አካል እንዲያስመዘግብ የሚመራ ከመሆን አልፎ ውሉን ፍርስ የማድረግ ውጤት የለውም፤ ውጤቱም ቢሆን በ1723 ላይ አለመገለፁ ለዚህ ጠቋሚ ነው ማለት አለብን? እርስዎ የትኛውን ይደግፋሉ?

2. አንድ ውሉ በ1720 መሰረት እንደረቂቅ ይቆጠራል በማለት እና ውሉ እንዲከተል የታዘዘውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተሉ ፍርስ ነው በማለት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? አንድ ውል ፍርስ ነው ሲባል ከመሰረቱ እንዳልተሰራ ይቆጠራል?

3. መኖሪያ ቤትን የማከራየት ስምምነት በጽሁፍ ያልተደረገ እንደሆነ ውሉ ፍርስ ይሆናል? (ኪቤአድ እና ሶስና አስፋው)

4. የኢንሹራንስ ውል በጽሁፍ ካልተደረገ ፈራሽ እንደሆነ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1725 ላይ ተገልጿል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሳሊኒ እና አዋሽ ኢንሹራንስ ጉዳይ ላይ የኢንሹራንስ ውል ለረጅም ጊዜ የሚደረግ ካለሆነ በቀር በጽሁፍ እንዲደረግ አስፈላጊ አይደለም ህጉ አያዝም የሚል አቋም ወስዷል እርስዎስ ይህን አቋም እንዴት ያዩታል? በተመሳሳይ አቋም የዋስትና ውልም ለረጅም ጊዜ የተደረገ ካለሆነ በቀር የግድ በጽሁፍ እንዲደረግ አልታዘዘም ማለት ይቻላል? አስተያየትዎን ይስጡበት፡፡

   በዚህ ዙሪያ የህጉ ዓላማ ዳኞች ለረጅም እና ለአጭር ጊዜ የተደረጉትን እየለዩ እንዲሰሩ ፍላጐት አለው? ድንበሩስ እንዴት ለመወሰን ይቻላል? ነው ወይስ ህጉ ለረጅም ጊዜ የተደረጉ ውሎች በማለት በ1725 ላይ ሲገለጽ ከዚያ በላይ የተገለፁትን ዝርዝሮች ለረጅም ጊዜ እንደተደረጉ ውሎች ደምድሟል (has presumed) እንበል? የትኛው ትክክል ይመስልዎታል?

5. ከ500 ብር በላይ ያለን ብድር በጽሁፍ ካልተደረገ በቀር ፈራሽ ይሆናል? ካልሆነ ከብር 500 በላይ በብድር መውሰዱን ገልጾ የፈረመበት ሰነድ በሁለት ምስክሮች አለመረጋገጡ በማስረጃነት የቀረበውን ሰነድ ፍርስ ያደርገዋል? (see ታደሰ እንዳይላሉ እና ብርሃኑ እሸቱ)

6. በአንድ ወቅት አንዲት ሴት ከባንክ በብድር ገንዘብ ሲወስዱ መሐመድ ዋስ ሆኗቸዋል፡፡ በዋስትናም ከፈረመ በኋላ ይኸው ሰው ከተደዳሪዋ ወ/ሮ አበበች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመክፈል የተስማሙ ቢሆንም ለዋሱ አስጊ ሁኔታን ላለመፍጠር በስድስት ወር ሲከፍሉ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከፍለው የማይጨርሱ ቢሆን የቡና ቤት የንግድ ድርጅታቸው ለዋሱ ለማስረከብ ይስማማሉ፡፡

   ለዋሱ ቃል በገቡለት መሰረት ብድሩን በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አልከፈሉም፡፡ አንዱ ዓመትም እያለፈ በመሆኑ ለዋሱም ሆነ ለባለዕዳዋ ከባንክ ማስጠንቀቂያ ይደርሳቸዋል፡፡ ይከሰሳሉ፡፡

   ዋሱ ከወ/ሮ አበበች ጋር በነበረው ስምምነት መሰረት የቡና ቤቱ ድርጅት ስመንብረትነት ይዛወርልኝ የሚል ክስ ያቀርባል፡፡ ሴትዮዋም ባንክ የአንድ ዓመት ጊዜ ሰጥቶኝ እያለ ዋሱ በስድስት ወር መክፈል አለብሽ ብሎ ማስፈረሙ ትክክል አይደለም ፍርስ ነው ብላ ተከራከረች፡፡ ፍርድ ቤቱም ግዴታዋን በማክበድ ውለታ ውስጥ ገብታለች ከሚባል በቀር ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ ምክንያት የለም ብሎ ስም እንድታዛውር ወሰነ፡፡

   ጉዳዩ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከታየ በኋላ ወ/ሮ አበበች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ያደረጉት ውል በርሳቸውና በባንኩ መካከል ህግ ነው (1231)፡፡ ይህን ህግ በመቃረን የሚደረግ ስምምነት ደግሞ ህገ ወጥ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ውሉ ህገ ወጥ ስለሆነ ማስፈፀም አይቻልም ብሎ ወሰነ፡፡ በይግባኝ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አፀናው፡፡

   አንድ ውል ህገ ወጥ ነው ማለት ምን ማለት ነው? የፍርድ ቤቶቹ መደምደሚያ ትክክል ነበር ብለው ያስባሉ? ለምን?

7. በሁለት ሰዎች መካከል የብድር ውል ተፈርሟል፡፡ ብድሩ ባለመከፈሉ ክስ ቀረበ፡፡ ብድሩ አልተከፈለም በሚል ለቀረበበት ክስ ተበዳሪው አልተበደርኩም አይልም፡፡ ነገር ግን በውሉ ላይ የፈረምኩት እኔ ብቻ ነኝ በውሉ ላይ ደግሞ መፈረም ያለበት በሁለታችንም ነው፡፡ ይህን የማያሟላው የጽሁፍ ማስረጃ ፍርስ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ እርስዎስ ያለዎት ሀሳብ ምንድንው?

8. በህግ የተደነገገውን የአፃፃፍ ሥርዓት ያልተከተለ ውል አለ። ይህን ውል መሰረት በማድረግ ክስ የቀረበበት ባለዕዳ ውሉ የአፃፃፍ ሥርዓቱን ያልተከተለ ውል ስለሆነ አልገደድበትም በማለት ይከራከራል።

   ባለገንዘቡ በበኩሉ ውሉ እንዲፈርስለት ክስ ማቅረብ የነበረበት በሁለት ዓመት (1810) ውስጥ ነው። በዚህ ጊዜ ውሉን ያላፈረሰ በመሆኑ በጊዜ ሂደት ውሉ የፀና ሆኗል። የፀና ውል ደግሞ መፈፀም ስላለበት ሊከፍለኝ ይገባል ከዚህ በተጨማሪም ወሉ አስር ዓመት ያልሞላው በመሆኑ ይክፈለኝ በማለት ይከራከራል። ምን አቋም አለዎት? የማን ክርክር ተቀባይነት ያለው ይመስልዎታል።

9. ብዙ ጊዜ በፍርድ ቤቶች እንደሚታየው የአንድ ውል የአፃፃፍ ሥርዓቱን ተከትሎ መሠራት አለመሠራት ጭብጥ ሆኖ ሲቀርብ የሚጠየቀው ሥርዓት አልተሟላም ብሎ ፍርድ ቤቱ ያመነ እንደሆነ ውሉን ፍርስ በማድረግ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ሁኔታ እንደመለሱ ያደርጋል። ግን ሌላ አማራጭ አይኖርም? ካለ መቼ እና በምን ሁኔታ መጠቀም አለብን?

10. አቶ ሙላቱ ለአቶ ሁነኛው ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) ያበድራሉ። የመመለሻው ቀን ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ነው። በዚህ ጊዜ ባይመልሱ በየወሩ ብር 30 ወለድ እየታሰበ ሊከፈል ተስማምተዋል። አልፈከፈለም።

    አቶ ሙላቱ ክስ መሠረቱ። አቶ ሁነኛው ውሉ ህገወጥ ስለሆነ አልጠየቅበትም በማለት ይከራከራሉ። ይህን የሚሉት ወለዱ ህገ ወጥ ነው በማለት ነው። እርሶ ዳኛ ቢሆኑ ምን ይፈርዳሉ?

11. ገብሩ ገ/መድኀን ቄስ ገ/መድኀን ረዳ በስልክ ብር እንዳበድራቸው ጠይቀውኝ በኢትዮጵያ

    ንግድ ባንክ በኩል ብር 50 000 ልኬላቸው ተቀብልዋል ነገር ግን ሊመልሱልኝ ያልቻሉ

    ስለሆነ ይክፈሉኝ በማለት ክስ አቀረበ።

    አቶ ገ/መድኀን በበኩላቸው ብር 50 000 መቀበላቸውን ያምናሉ የሚከራከሩት ይህ

    ገንዘብ ቀደም ሲል እኔ አበድሬያቸው ስለነበር ስለብድሩ የተሰጠኝ ክፍያ ነው በማለት ነው።

    ገንዘብ አበድሬለሁ ካሉ ስለማበደራቸው የፅሁፍ ማረጋገጫ ሊያቀርቡ ይገባል፤ ከባንክ

አግኝቼዋለሁ የሚሉት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሰጥቼዋለሁ ለሚሉት ብድር ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም ይላሉ፡፡

ፍርድ ቤቱም ቂስ ገ/መድኅን ብር 50 000 መቀበላቸውን አልካዱም፤ ይህን ገንዘብ የተቀበሉት ቀደም ሲል ሰጥቼው ነበር ለሚሉት ብድር ከሆነ ማበደራቸውን በቅድሚያ ማስረደት ያለባቸው እሳቸው ናቸው፤ በአዎንታዊ መልኩ የሚከራከር ሰው የክርክሩን ፍሬ ነገር ማስረዳት ይገባዋል፡፡ ይህን ሳያደርጉ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወስናል፡፡

በፍርዱ ላይ የተሰጠውን ትችት እንዴት ያዩታል? አስተያየትዎን ይስጡበት፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የውል አለመፈፀም ደንብ

**የሥልጠናው ጠቅላላ ዓላማ**

ሠልጣኞች ከሥልጠናው በኋላ፣

- በውል አለመፈፀም ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን ይለያሉ፡፡
- በውሉ አለመፈፀም ምክንያት የተጎዳ ሰው ያለውን አማራጭ ይለያሉ፡፡
- ውል ያልተፈፀለት ሰው ሊኖረው የሚገባውን ጥንቃቄ ይገነዘባሉ፡፡

**የሥልጠናው ዝርዝር አላማዎች**

ሠልጣኞች ከውይይቱ በኋላ፣

- ውልን በግዴታ ማስፈፀም የሚቻልበትን ሁኔታ ይለያሉ፡፡
- በኪሳራ አከፋፈል ረገድ የውል እና ከውል ውጪ ህጎች ያላቸውን ግንኙነት ይገነዘባሉ፡፡
- የጉዳቶች ዓይነቶችን ይለያሉ፡፡
- የኪሳራ ዓይነቶችን ይለያሉ፡፡
- በኪሳራ አከፋፈል ረገድ ዳኛ ሊኖረው የሚገባውን ሚና ይለያሉ፡፡

## 4. የውል አለመፈፀም ደንብ

ሰዎች የውል ግዴታ ውስጥ የሚገቡት በአንድ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ምክንያታቸው እንዲሳካ ይፈልጋሉ፡፡ የሚያስገኝላቸውን ጥቅም ያስባሉ፡፡ የሀብት ልውውጥ በራሱ አንድ ዓይነት የኢኮኖሚ ጥቅምን ያስገኛል፡፡ የበለጠ ገንዘብ ለማትረፍም ይረዳል፡፡ ጥሬ ሀብቶች ወደሚፈለጉበት ውጤት የሚቀየሩት በዚሁ መንገድ ነው፡፡ ምርታማነት ይበረታታል፡፡ ነገር ግን ይህ እንዲሆን የሰዎችን መተማመን ለማትረፍ በሚችል ደረጃ የውል ግንኙነት ጥበቃ ያስፈልገዋል፡፡ ልውውጥ ቀና የሚሆነው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ለውል ጥበቃ መደረጉ የተገባ ነው፡፡ ሰው በቃሉ ይታሰራል የሚለው ብሂልም የዚህ መሠረታዊ ሀሳብ ነፀብራቅ ነው፡፡

ይህ ቢሆንም ታዲያ በተለያዩ ምክንያቶችውል አፈፃፀም ችግር ሊገጥመው ይችላል፡፡ አንዱ ወይም ሌላው ተዋዋይ ውሉን ለመፈፀም የማይችልበት ወይም የማይፈልግበት ምክንያት ሊፈጠር ይችላል፡፡ እንዲህ ሲሆን የህጉ ጥበቃ ትርጉም የሚያገኘው ውሉን ያላከበረው ወገን የገባበትን ስምምነት በግዴት እንዲፈፅም ወይም ውሉ ላልተፈፀመለት ሰው ካሳ እንዲከፈለው በማድረግ ነው፡፡ ውሉ የፈረሰበት ወገን ከነዚህ ምርጫዎች ውስጥ አንዱን በመውሰድ መብቱን ለማስከበር ይችላል፡፡ የሁሉንም አሠራር እንደየቅደም ተከተሉ የምናየው ይሆናል ፡፡

### 4.1 ውል በግዴታ እንዲፈፀም ስለመጠየቅ

እንዲህ ያለው መፍትሄ ውሉ የፈረሰበት ወገን መብት በተሻለ መንገድ የሚያስጠብቅ ነው፡፡ የባለዕዳውን ፈቃድ ማግኘት ሳያስፈልግ በፍርድ ሀይል በስምምነቱ መሠረት ቃል የተገባውን አንድ ነገር ለማስገኘት ይረዳል፡፡ ውሉ በፈቃድ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ውሉ የፈረሰበት ወገን ይገኝ የነበረበት ቦታ ላይ የሚያስቀምጠው  ይሆናል፡፡

ርግጥ መብቱን ሁልጊዜም በቀላሉ የምናገኘው አማራጭ አይደለም፡፡ ለምሳሌ አንድን ምርት በአንድ የተወሰነ ጊዜ ለማቅረብ ግዴታ የገባ ሰው ቃሉን ለማክበር ሳይችል ወይ ሳይፈልግ ቀርቷል እንበል፡፡ ውሉ የፈረሰበት ሰው ውሉ በግዴታ እንዲፈፀምለት ይፈልጋል፡፡በክርክሩ ሂደት ግን ምርቱ ከዓለም ገበያ ይጠፋል፡፡ እንዲህ ሲሆን ውሉን በግዴታ ለማስፈጠም አይቻልም፡፡ ሌላ አማራጭ በመጠቀም ውሉ የፈረሰበት ወገን ካሳ እንዲያገኝ ከማድረግ በቀር በጥያቄው መሠረት ለማስተናገድ ያስቸግራል፡፡ ይህ ማለት አንድ ውል ለመፈፀም የማይቻል መሆን ይህንን መፍትሄ ለመጠቀመም ያለንን ዕድል ያጠባል ማለት ነው፡፡

ሌላው ውሉን በግዴታ ለማስፈፀም የባለዕዳውን ፈቃደኝነት የሚያስፈልግበት አጋጣሚ መኖር ነው። እርሱ ያልፈቀደ እንደሆን መፍትሄውን በአማራጭነት ለመጠቀም የባለዕዳው ነፃነት የሚነካበት ሁኔ ይፈጠራል። ለምሳሌ ሥዕል ለመሳል የተስማማ ሰው ሃሳቡን ቢሠርዝ በፍርድ ኃይል ሥዕል ሠርቶ እንዲያስረክብ ማድረግ አይቻልም። በግዴታ ውስጥ ያለ ሰው በነፃ አዕምሮው የፈጠራ ክህሎቱን ተጠቅሞ ውጤት ያለው ሥራ ይሠራል ተብሎ አይታሰብም። ስለሆነም ማስገደዱ በአንድ በኩል ሰዎች ነፃ ሆነው የማሰብን የመሥራት መብታቸውን የሚነካ  በሌላ በኩል ተፈላጊውን ውጤትም የሚያስገኝ አይሆንም። እንዲህ ባለ ሁኔታ ይህን መፍትሄ መተቀም አስቸጋሪ ይሆናል። የፍ.ህ.ቁ. 1776 እና 1777 (1) ።

ከዚህ በቀር ውልን በግዴታ ለማስፈፀም ሁለት ነገሮች መሟላታቸውን ማረጋጥ ይጠይቃል። አንዱ የውሉ መፈፀም ለባለገንዘቡ የተለየ ጥቅም የሚሰጠው መሆኑን ነው። በህግ ግምት ካልተወሰደበት በቀርይህን ማስረዳት የሚተበቅበት ባለገንዘቡ ነው። ሁለቱ የማይነጣጠሉ በአንድነት መታየት ያለባው ነጥቦች ናቸው። የነኚህ ሁኔታዎች መሟላት ነው ባለገንዘቡን የመፍትሄው ተጠቃሚ የሚያደርገው።

## 4.2 ውል እንዲሠረዝ ስለመጠየቅ

ከፍ ሲል የተጠቀሰውን መፍትሄ መጠቀም የማይችል ሰው ውሉ እንዲሰረዝና በምትኩም ካሳ እንዲከፈለው ለመጠየቅ ይችላል። ይህ ሁለተኛው አማራጭ መሆኑ ነው። የካሳው ክፍያ ጥያቄ እንደሚከተለው በሁለት መንገድ ሊቀርብ ይችላል።

### 4.2.1 በፍርድ የሚወሰን ኪሳራ

ውል ሲፈርስ በተዋዋዮች ላይ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል። የተጎዳ ሰው ሲኖር ደግሞ ጉዳቱ ሊጠገንለት ይገባል። ይህ በሁሉም የህግ ሥርዓቶች ያለ በፍትህ መሠረት ላይ የቆመ አሠራር ነው። የካሳውን መጠን በተመለከተ በመርህ ደረጃ ከደረሰው ጉዳት ጋር የተመዛዘነ መሆን አለበት። The principle of equivalence ይባላል።

እንደሌሎች ሁሉ የኢትዮጵያ ህግም ለደረሰ ጉዳት ሊከፈል የሚገባው ካሳ ከጉዳቱ ጋር የተመዛዘነ መሆን እንዳለበት ይቀበላል። የፍ.ህ.ቁ. 2190 የሚነግረንም ይህንኑ ነው። ከውል መፍረስ ጋር በተያያዘ ሊከፈል የሚገባው ካሳም ከውል ውጪ ለሚደርስ ኃላፊነት በሚከፈለው ዓይነት

እንደሚመራ በፍ.ህ.ቁ. 1790 (2) መገለፁ የዚህ መርህ ተፈፃሚነት በውል ግንኙነቶችም ላይ እንደሚሆን የሚያጠይቅ ነው፡፡

ርግጥ የህጉን ዝርዝር ይዘት ስንመለከት ሁኔታዎች በመጠኑ የተለዩ ሆነው እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ የፍ.ብ.ህ.ቁ. 1799 ከፍ ሲል ከተተቀሰው መርህ በመለየት የካሳ ክፍያውን መጠን አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው የውሉ አለመፈፀም ያደርሳል ብሎ በሚገምተው አስተያየት ልክ እንደሚሆን ይገልፃል፡፡ ፍርድ ቤቶች የመንሽራሸር ነፃነታቸውን ትርጉም ባለው መንገድ እንዲጠቀሙበት ይረዳ ዘንድ ህጉ ከግምት መግባት ያለባቸውን ዝርዝሮች በአመልካችነት ጠቁሟል፡፡የውሉ ዓይነት፣ የተዋዋዮች የሞያ ሥራ፣ ቀደም ሲል የነበራቸው ግንኙነት፣ ባለዕዳው የሚያውቃቸው ሁኔታዎችና ማንኛዎቹም አጋጣሚዎች ሚዛናዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ያስችላሉ የተባሉ ነጥቦች ናቸው የፍ.ህ.ቁ. 1799 (2) ፡፡

የህጉ መለኪያ አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው አስተያየት መሆኑን ቢገልፅም ዕዳውን የሚያከብዱ ልዩ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ባለገንዘቡ አስታውቆት እንደሆነ፣ ጉዳቱ የደረሰው ባለዕዳው ሆነ ብሎ ባለገንዘቡን ለመበደል ባደረገው ተግባር ምክንያት ወይም ባሳየው ጉልህ ቸልተኝነት እንደሆነ ወይም የደረሰው ጉዳት አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው ከገመተው መጠን በታች መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ የካሳው ክፍያ በደረሰው ዕርግጠኛ ጉዳት ልክ ይሆናል (የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1800 እና 1801) በማለት ወደቀደመው የጉዳት ካሣ ተመዛዛኝነት መርህ መልሶ ይወስደናል፡፡ በዚህ መሠረት ዕርግጠኛ የጉዳት ካሳ ክፍያውን ያገኛል ማለት ነው፡፡

ዕርግጠኛውን የጉዳት ካሳ ግን በማንኛውም ሁኔታ የሚያገኝ አይደለም፡፡ ተበዳዩ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በሚያደርገው ጥረት ይወሰናል፡፡ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማሳነስ በርሱ በኩል ሊፈፅመው ወይም ሊቆጣጠረው ይችል የነበረ ተግባር ካለ ተባዳዩ ይህን ለመቆጣጠር መትጋት አለበት፡፡ በቸልታው ምክንያት ጉዳቱ ቢበዛ ሊያርቀው ይችል በነበረው ጉዳት መጠን የሚደርሰውን ኪሳራ ራሱ እንዲሸከም ይገዳደል፡፡ ለምሳሌ አበበ በምርት ሂደት የሚያስፈልገውን አንድ ጥሬ ዕቃ ሱራፌል ሊያቀርብለት ስምምነት አድርጓል፡፡ ሱራፌል ግዴታውን እንደማይወጣ አበበ ተረድቷል፡፡ ይህን እንዳወቀ “ምንቸገረኝ ኪሳራዬ እንደሁ አገኛለሁ” ብሎ ቸል ቢል ኂላ ጥሬ ዕቃው ባለመቅረቡ ምክንያት የደረሰበትን ኪሳራ ሁሉ መጠየቅ አይችልም፡፡ ጉዳቱን ለመቀነስ ማድረግ የሚገባው ያንኑ ጥሬ ዕቃ ከገበያ ላይ ፈልጎ ማግኘት የሚችል ሲሆን መተካትና ሥራውን ማከናወን ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ኪሳራውን መቀነስ ይችላል፡፡ ከዚያ በተረፈ ይህን ዓይነት የጥንቃቄ ዕርምጃ ያልወሰደው

ጥረቱ አስቸጋሪና ብዙ ወጪን ስለሚያስከትልበት መሆኑ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ አሊያ ግን ሊያርቀው ይችል በነበረው መጠን ካሳውን እንዳያገኝ ህጉ ያግደዋል፡፡ ጉዳት እንዳይበዛ ቸልታም እንዳይኖር የሚረዳ ማትጊያ ነው (in economic terms it is an incentive)፡፡

አጠቃላይ ስለሆነው የካሳ ክፍያ ይህን ካልን አሁን ደግሞ ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት ስለሚደርሱት የጉዳት ዓይነቶች እናያለን፡፡ እንደሚከተለው በሦስት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

### *ሀ. በውሉ ለማግኘት የታሰበውን ተስፋ በማጣት የሚደርስ ጉዳት (loss of expectation)*

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በውል ግንኙነት ውስጥ ያሉ ተዋዋዮች በየራሳቸው ከውሉ እናገኛለን ብለው የሚያስቡት ጥቅም አለ፡፡ አንዱ ተዋዋይ ውሉን ለመፈፀም በማይችልበት ወይም በማይፈልግበት ጊዜ ሌላው ተዋዋይ ከውሉ ማትረፍ ይፈልግ የነበረውን ተስፋ ያጣል፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች የፀና ውልን በመተማመን ለሚደርስባቸው ጉዳት ህጉ ዋስትና ይሰጣል፡፡ ይህም ካሣ እንዲያገኙ በማድረግ ይተረጐማል፡፡ ተዋዋዮቹ በየበኩላቸው የሚፈለግባቸውን ግዴታ ተወጥተው ውሉ ተፈፅሞ ቢሆን ኖሮ አንድ አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው ተበዳዩ ሊደርስበት/ሊያገኝ ይችል ነበር ብሎ በሚሰጠው አስተያየት መነሻነት ተበዳዩ ቀርቶበታል የተባለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማስላት ነው፡፡

በምሳሌ ለመግለጽ ያህል ዓለማየሁ በብር 45,000 ሊሸጣት ያሰባት አንዲት ቶዮታ ኮሮላ መኪና አለችው፡፡ በቀለ በተመጣጣይ ዋጋ እንዲህ ያለች መኪና ማግኘት እንደማይችል በማሰብ የተሰጠውን ዋጋ ይቀበላል፡፡ ውሉ ከተፈፀመ በኋላ ዓለማየሁ መኪናዋን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ እንደሚችል በማሰብ ገዢ አፈላልጐ በብር 65,000 ይሸጣል፡፡ በቀለ ውሉ ስለፈረሰበት ዓለማየሁን ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ይከሳል፡፡ ለበቀለ መከፈል ያለበት የጉዳት ካሣ የሚሰላው አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው ውሉ በተመሠረተ ጊዜ የመኪናው ዋጋ ርክክብ በሚደረግበት ጊዜ ምን ያህል እንደሚሆን በሚሰጠው አስተያየታዊ ግምት መነሻነት የሚሰላ ነው፡፡ በዚህ ሰው አስተያየት የመኪናዋ ዋጋ ብር 70,000 ይገመት የነበረ ከሆነ በቀለ የደረሰበት ጉዳት 70,000 ሲቀነስ እሱ መኪናዋን ለመግዛት የተስማማበት ዋጋ ብር 45,000 = 25,000 ይሆናል ማለት ነው፡፡

በሌላ ምሳሌ ለማብራራት አንድ የታክሲ ባለቤት ለሌላ የታክሲ ባለቤት አንድ በታክሲ አገልግሎት ልትሠማራ የምትችል ሚኒ ባስ በብር 70,000 ሸጠለት፡፡ ዓለማየሁ መኪናውን በተሻለ ዋጋ የሚገዛው ሰው በማግኘቱ ከበቀለ ጋር ያደረገውን ውል ያፈርሳል፡፡ በቀለ ለጉዳቱ ካሣ እንዲከፈለው ይጠይቃል፡፡ የዚህ ሰው የጉዳት ካሣ ውሉ ተፈፅሞ ቢሆን ኖሮ ሊያገኝ ይችል የነበረው ጥቅም ነው፡፡ እሱም

- የመኪናውን ዋጋ በተመለከተ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የደረሰበት ጉዳት
- መኪናዋን በታቀደው ጊዜ አግኝቷት ቢሆን ኖሮ በታክሲ አገልግሎት ላይ አሠማርቶ ያገኝ የነበረው ጥቅም አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው በሚሰጠው አስተያየት ልክ ይሆናል ማለት ነው፡፡

### ለ. ውልን በመተማመን ምክንያት የሚደርስ ጉዳት

ሰዎች የውሉን ቃል ወይም ተፈፃሚነቱን በመተማመን ለተጨማሪ ወጪዎች የሚዳረጉበት ሁኔታ አለ፡፡ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ምሳሌ በቀለ የተደረገውን ውል በመተማመን ለመኪናዋ ይሆናል ብሎ ያሰበውን አራት ብሪጂስቶን ጐማ እያንዳንዱን በብር 8,000 በድምሩ በብር 32,000 ገዝቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ወጪው የተደረገው የውሉን መከበር በመተማመን ነው፡፡ ውሉ በሌላው ተዋዋይ ሲፈርስ ለመኪናዋ ሲል ያወጣው ብር 32,000 ኪሣራ ይሆንበታል፡፡ ማንኛውም ሰው የመሠረተውን ውል በመተማመን በሚያከናውናቸው ተግባራት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ውሉን ያፈረሰው ወገን ይህንን ጉዳት መካስ ይገባዋል፡፡ ውሉን በመተማመን በአንድ ተዋዋይ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት ይህ ነው፡፡

### ሐ. በውል ምክንያት ከአንዱ ወደ ሌላው በተላለፈ ሀብት ምክንያት የሚደርስ ጉዳት

ውል በመደረጉ የተነሣ አንዱ ለሌላው ያስተላለፈው ሀብት ወይም የፈፀመው ከፊል ክፍያ ሊኖር ይችላል፡፡ ውሉን ሌላው ተዋዋይ ሳያከብር ሲቀር ሀብቱ ባፈረሰው ሰው እጅ ይቀራል፡፡ በዚሁ መጠን ጉዳት ይደርሳል፡፡ ስለሆነም የተወሰደው ንብረት የተከፈለው ገንዘብ እንዲመለስ በማድረግ ጉዳቱ ይጠገናል፡፡

ስለሆነም በተራ ቁጥር ለ እና ሐ የሚደርሱ ጉዳቶች ተዋዋዩን ውሉ ከመፈፀሙ በፊት እነበረበት ቦታ ላይ የሚያስቀምጡት ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

### 4.2.2 በተዋዋዮች በቁርጥ የሚወሰን ኪሳራ (liquidated damage)

አንዳንድ ሰዎች ውል ሲመሰርቱ ውሉ ላይፈፀም የሚችልበትን ሁኔታም አስቀድመው ያያሉ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳት በማሰብ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት በሚደርስባቸው ጉዳት ላይ ስምምነት ያደርጋሉ፡፡ ወይም ተዋዋዩ ስምምነቱን እንዳይፈርስ ይረዳል ብለው የሚያስቡትን መቀጫ ሐረግ ባሉ ላይ ያስገባሉ፡፡

የመቀጫ ስምምነቱ ሁለት መልክ ሊኖረው ይችላል፡፡ አንዱ ተዋዋዮቹ ይደርሳል ብለው ያሰቡትን ገንዘብ ኪሳራ ልክ የሚወስኑበት ነው፡፡ It is compensatory፡፡ ርግጥውሉ በተሠረዘ ጊዜ የደረሰው ጉዳ ተዋዋዮች አስቀድመው ከወሰኑት መጠን ያነሰ ወይ የበዛ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና የሚያገኙት በስምምነታቸው መሰረት አንዱ ለሌላው ሊከፍል ያሰበውን ካሳ ነው፡፡ በበዛው ወይ ባነሰው መጠን የሚታየው ልዩነት ተዋዋዮች ኪሳራውን ለመካፈል እንደወሰኑ ያሰገምታል፡፡ ስለሆነም መብዛት ወየ ማነሱ ከግምት ሳይገባ የተስማሙበትን መጠን ውሉ ለፈረሰበት ወገን ይከፍላሉ፡፡

አስቀድመው መስማማታቸው በክርክር ሂደት መጠኑን በመወሰን ረገድ ያለውን ውስብስብ የማስረጃ ሂደት ያቀላል፡፡ ሊፈፀም ከሚችል ግድፈትም የሚጠብቅ ነው፡፡ ውሉ ቢሠረዝ የሚደርስባቸውን የካሳ ክፍያ መጠን እንዲያውቁ ዕድል በመስጠት በግንኙነታቸው ዕጣ ፈንታ ላይ ተገቢ ነው የሚሉትን ውሳኔ ለማሳለፍ ያስችላቸዋል፡፡ ለምሳሌ ይታይአንድ መጽሐፍ በብር 50 ሊገዛኝ ተስማምቷል፡፡በአምስት ቀናተወ ውስጥ ባላመጣለት ኪሳራ ብር 10 ልከፍለው ተስማምተናል፡፡ ቀለም ይህንኑ መጽሐፍ በብር 60 እገዛሃለሁ ብሎ ቀረበ፡፡ ለዚህ ሰው ብሸጥለት ከይታይ ጋር ያለኝን ውል በማፍረሴ ልከፍል ከምችለው ኪሳራ ብር 10 አንፃር ሲታይ ውጠየቱ ልዩነትን አይመጣም፡፡ ስለሆነም ውሉን ለማፍረስ ያለኝን ፍላጎት እሠርዛለሁ፡፡ ለኔ የሚያዋጣኝ ከብር 60 በላይ ሊገዛኝ የሚመጣ ሰው ያለ እንደሆን ነው፡፡ ለይታይ ካሳ ከፍዬም ቢሆን የተሸለ ጥቅም ማግኘት የምችለው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህን መወሰን የቻልኩት የመጀመሪያውን ውል ባፈርስ የሚጠበቅብኝን የኪሳራ መጠን በማወቂ ነው፡፡ ማንም ሰው ሳይጎዳ ሀብትን ወደተሻለ ተጠቃሚ ለማስተላለፍ ይረዳል ማለት ነው፡፡

የዚህ ዓይነቱ በውሉ ፋንታ የሚከፈለው የካሳ መጠን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት የሚክስ በሚገባ የሚክስ ነው፡፡ ስለሆነም ተዋዋዩ በጉዳቱ የሚደርስበትንካሳ ተቀብሎ ይሄዳል፡፡ ውሉ ይፈፀምልኝ ካሳውም ይከፈለኝ ብሎ መጠየቅ አይችልም፡፡

ሁለተኛው የመቀጫ ስምምነት ዓይነት ደግሞ በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተዋዋዩ ግዴታውን እንዲወጣ ለማስገደድ ወይም ለተጨማሪ ግዴታዎች መፈፀም ዋስትና እንዲሆን ተብሎ የሚወሰን ነው፡፡ ከፍ ሲል ከተተቀሰው መቀጫ የሚለየው ከዋናው ግዴ ጋር የሚፈፀም መሆኑ እና ዓላማው ተዋዋዩ ውሉን እንዲያከብር ለማስገደድ *[to secure performance]* መሆኑ ነው፡፡

በመጀመሪያውም ሆነ በሁለተኛው መንገድ በተዋዋዮች የሚወሰነው ኪሳራ እርግጠኛ ከሆነው የካሳ መጠን የበዛ ወይ ያነሰ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ምክንያት በማድረግ ግን ዳኞች መጠኑን ሊያሻሽሉት አይችሉም፡፡ ይሁንና ውል የተሠረዘበት ወገን ሳይጎዳ *[ተገቢውን ካሳ የሚያገኝ በመሆኑ]* ነገር ግን ሀብቱ ወደተሻለ ተጠቃሚዎች ሊያልፍ የሚችልበት አጋጣሚ ቢኖር ይህን ዓይነት የሽቀጥ ልውውጥ የሚገታ የካሳ መጠን ተደርጎ ቢሆን ፍርድ ቤቶች ምን ዓይነት ውሳኔ ማሳለፍ አለባቸው? ይህን መሠረት በማድረግ ውሉን ለማሻሻል አይቻላቸውም? ይቻላል ከተባለ ተዋዋዮቹ በነፃነት ለመዋዋል ባላቸው መብት ጣልቃ መግባት አይሆንም?

## መልመጃ

1. ሰኔ 20 ቀን 1978 ዓ.ም በተፈረመ የብድር ውል6 በሮች እና 4 መስኮቶች ሠርቶ ሐምሌ 11 ቀን 1978 ዓ.ም ለማስረከብ፣ በዚህ ጊዜ ባያስረክብ ያለምንም ክርክር ብር 3000 መቀጫ ለመክፈል አቶ ተመስገን ተስማምቷል፡፡ ጥሬ ዕቃውን የሚያቀርበው አሠሪው አቶ ዓለማየሁ ነው፡፡ ለዕጅ ዋጋ ደግሞ ብር 1100 ይከፈለዋል፡፡

   አራት መስኮቶችና አንድ በር በጊዝው ሠርቶ አስረክቧል፡፡ ቀሪ አምስት በሮች ባለማስረከቡ ክስ ቀረበበት፡፡ የክሱ ይዘት መቀጫውን ብር 3000 ከወለድ ከኪሳራና ከወጪ ጋር ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡

   ተከሳሹ አቶ ተመስገንበሰጠው መልስ ብር 3000 የሚያወጣ ዕቃ አልተረከበብኩም፤ 6

   በሮች እና 4 መስኮቶች ብቻ ይህን ያህል አያወጡም፡፡ ያስረከብኩት አንድ በር እና 4

መስኮት ስላለ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት። ስለዚህ ቀሪውን ሥርቼ ሳደርስ ይውሰዱ በማለት ተከራከረ።

ፍርድ ቤቱም ተከሳሹ መክፈል ከሚገባው መቀጫ ብር 3000 ውስጥ የአራት መስኮት እና የአንድ በር ዋጋ ተቀንሶ ቀሪውን ተከሳሹ ይክፈል በማለት ወሰነ።

በፍርዱ ላይ ያለዎትን አስተያየት ይስጡ?

2. ኤልያስ መጋቢት 24 ቀን 1983 ዓ.ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ከአቶ እንግዳሸት አጎናፍር ቤት ገዝቷል። ብር 5000 ቀብድ ከፍሏል። ውሉን የሚያፈርስ ወገን ብር 5000 መቀቸ እንዲከፍል ተስማምተዋል። እንግዳሸት ውሉን አፈረሰ። ኤልያስ መቀጫውን ብር 5000 ይክፈለኝ ፣ ቀብዱንም ይለቃል ብሎ መከራከር ይችላል?

3. በአንድ የተወሰነ ዕቃ ሠርቶ ለማቅረብ ግዴታ የገባ ሰው አቶ አበበ ዋስ ሆኗል። በተባለው ቀን ባያደርስ ብር 3000 መቀጫ ከፍሎ ሊያስረክብ ግዴታ ገብቷል። በጊዜው አላደረሰም።ዋሱ እና ባለዕዳው ተከሰሱ። ዋሱ የዋስትና ግዴታዬ ለዋናው ዕዳ አፈጻጸም እንጂ ለመቀጫው አይደለም ይላል። የርስዎ አተያየት ምንድነው?

4. ፋጡማ አዋድ ለፀሐይ ሹምዬ የመጠጥ ድርጅታቸውን ከነሙሉዕቃው በብር 67 500 ሸጠዋል። የሽያጭ ውሉን ያፈረሰ ወይም በውሉ መሠረት ለመፈፀም ያልፈቀደ መቀጫ ብር 6000 ይከፍላል ብለው ተስማምተዋል። ገዢዋ ሻጭ ስም ለማዛወር አልፈቀዱም። ስለዚህ ብር 6000 መቀጫ ከፍለው ስም እንዲያዛውሩ ይወሰንልኝ በማለት ከሰሱ። ፍርድ ቤቱም ሻጭ ድርጅቱንማስረከባቸው በከፊል ግዴታቸውን እንደተወጡ ያሳያል። ገደቡ የተቀመጠው ለግዴታው መዘግየት ነው። በከፊል ግዴታቸውን ስለተወጡ ከብር 6000 ላይ ተቀንሶ ብር 2500 ብቻ ይክፈሉ፤ የደድርጅቱን ስመ-ሃብትነት ያዛውሩ ብሎ ወሰነ። መቀጫው የተቀመጠው ለውሉ መፍረስ ነው ወይስ ለግዴታው መዘግየት? በከፊል ተፈፅሟል ለተባለ ግዴታ ከብር 6000 ወደ ብር 2500 ለመውረድ መነሻው ምንድነው? ፍርድ ቤ በመቀጫው ላይ ወለድ ታስቦ ይከፈል ብሏል። የተፈረደበት በገን ደግሞ በመቀጫ ላይ ወለድ አይታሰብም ይላል። እርስዎ ምን ይላሉ?

5. ሌንጮ ዘገየ ሰኔ 12 ቀን 1982 ዓ.ም በተፈረመ የብድር ውል ብር 160 997 ለአቶ አብዱራህማን አበድሯል።ገንዘቡ መስከረም 6 ቀን 1983 ዓ.ም መመለስ አለበት በዚህ ጊዜ ባይመለስ ብር 10 000 ገደብ ለመክፈል ተስማምተዋል። በዚህ ጊዜ አልተከፈለም። ከሳሽ ሌንጮ ዘገየ ዋናውን ገንዘብ እና መቀጫውን አቶ አብዱራህማን ይክፈለኝ በማለት ይጠይቃል። ይችላል?

6. ዓለም ፀሐይ ትኩዕ የመኖሪያ ቤቷን በብር 43 000 ለደብረወርቅ ወልደ ልዑል ትሸጣለች። ቀብድ ብር 10 000 ተቀብላለች። ቤቱን አላስረከበችም። ደብረወርቅ ቤቱን ታስረክበኝ ብላ ትከሳለች። ዓለም ፀሐይ በበኩሏ የቀብዱን አጠፌታ ከፍዬ ውሉን ማፍረስ ስለምችል አላስረክብም ፣ ገንዘቧንም ትውሰድ፣ ተገድጄ ውሉን ልፈፅም አይገባም በማለት ትከራከራለች። ቀብድ መክፈል ውሉን በግዴታ ከማስፈፀም ይልቅ ውሉን በቀጥታ ለማፍረስ መብት ይሰጣል? በሌላ አባባል የቀብድ መኖር ውልን በግዴታ የማስፈፀም መብትን ያስቀራል?

7. ውል ያፈረሰ ውሉ ለፈረሰበት ወገን ብር 10 000 ለመንግስት ብር 20 000 የሚሉ ስምምነቶች ይደረጋሉ። ተዋዋዩ ውሉን ያፈረሰ ቢሆን ለመንግስት ይከፍላል የተባለውን ብር 20 000 እንዲከፍል ሊወሰንበት ይችላል?

8. ፈቃዱ ዳሌሮበብር 58 000 ለንጉሴ ወርቁ ቤት ሸጧል። ንጉሴ ብር 50 000 ከፍሎ ቤቱን ተረክቧል። ብር 8 000 ይቀርበታል። ሻጭ አቶ ንጉሴ ብር 8 000 ያልተከፈለኝ ስለሆነ ውሉ ይሰረዝልኝ በማለት ይጠይቃል። ውሉ በዚሁ ምክንያት መፍረስ አለበት?

9. ፋንታሁን በቀለ መኖሪያ ቤቱን ለበላይ ሙልዬ በብር 65 000 ለመሸጥ ተስማምቶ ይፈራረማል። በላይ የሚፈለግበትን ገንዘብ በስድስት ወር ውስጥ ሲከፍል ቤቱን ይረከባል። ስምምነቱ እነደተፈጸመ ብር 20 000 ተከፍሏል። ይሁንና ይህንኑ መኖሪያ ቤቱን በብር 170 000 የሚገዛው ሰው ስላገኘ የመጀመሪያውን ውል አፍርሶ ለጥበቡ ይሸጥለታል። አቶ በላይ አቶ ፋንታሁንን ምን ብለው ሊጠይቋቸው ይችላሉ? በአቶ ጥበቡ ላይ ኪሣራ ይክፈለኝ ብለው ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ? አቶ ጥበቡስ ምን ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ?

10. አቶ ይትባረክ ካሕሳይ ከጌራ ወርቅ ሁለት የጭነት መኪና ተከራይቶ ሲሠራ አንዱ መኪና ተገለበጠ። መኪናው ጉዳት ሲደርስበት ባለቤቱ አስጠግኖ ለተከራይ የማስረከብ ግዴታ

አለበት፡፡ አቶ ይትባረክ መኪናውን ወ/ት ጌራወርቅ አስጠግና ያልሠጠችኝ በመሆኑ በመኪናው ሠርቼ ላገኝ እችል የነበረው የብር 252 246 ጥቅም ቀርቶብኛል ይላል፡፡ ቀረብኝ የሚለው ይህንን ገንዘብመጠየቅ ይችላል? ወ/ት ጌራወርቅ ምን ዓይነት መከራከሪያ ማንሳት ትችላለች?

11. አቶ በላይነህ በለጠ ከአቶ አስፋው ዘውዴ ሰኔ16 ቀን1976 ዓ.ም.ብር 10 000 ተበድረው አልከፈሉም፡፡ ከተበደሩበት ቀን ጀምሮዋናውን ገንዝብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ክስ ቀረበባቸው፡፡ ተከሳሹም ወለድ ለመክፈል አልተስማማሁም፤ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ መክፈል የለብኝም በማት ይከራከራሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም የመክፈያ ጊዜው አልተከፈለም፤ ማስጠንቀቂያ ምስጠት ያስፈልግ ነበር፤ የሆነ ሆኖ ተከሳሹ ዋናውን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰበው ወለድ 9% ጋር ይክፈል በማለት ወሰነ፡፡ ትክክል ነው ብለው ያስባሉ? ማስጠንቀቂያ ያለመስጠት ውጤቱ ምንድነው?

## ምዕራፍ አራት

## ዋስትናዎች

በዕለት ተዕለት ግንኙነቶቻችን ውስጥ ሰዎች በውል የገቡልንን ግዴታ የሚወጡ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሊገባን ይችላል፡፡ ንቁ ሆነንም ሊደርስብን የሚችለውን ኪሳራ ሊተካልን የሚችል ማረጋገጫ ለማግኘት እንተጋለን፡፡ ካላገኘን ውል ለመፈጸም የነበረንን ውሳኔ እንሰርዛለን፡፡ በድፍረት ከገባንም ዕዳውን ለማስመለስ ያለንን ዕድል ልናጣ እንችላለን፡፡ እንዲህ ያለው ጥርጣሬ ቀና ለሆነ የንግድ ልውውጥ ሂደት እንቅፋት ነው፡፡

ስለሆነም ህጉ ቀና የሆነ የሸቀጥ ልውውጥን በማበረታታት የሚፈለገው የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲኖር የፈጠረው አንድ መሳሪያ ዋስትና ነው፡፡ ዋስትና በውል ግዴታ የገቡልን ሰዎች ቃላቸውን አክብረው እንደሚፈጽሙ ሦስተኛ ወገኖች ባለገንዘብ ለሆንነው ለኛ መተማመኛ የሚሰጡበት፣ ስለእነርሱ ሆነውም ግዴታውን ለመወጣት የሚስማሙበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ባለገንዘብ ለሆነ/ለሚሆን ሰው

ዕዳ ከፋይ ከሆነ አንድ ሰው ይልቅ በርካታ ሰው ዕዳ ከፋይ በማድረግ ገንዘብ የማስመለስ ዕድላችንን ያሰፋዋል፡፡ በልውውጡ ላይ ያለንን ዕምነትም ያሳድጋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ግዴ የመግባት ሥርዓት በአብዛኛው ከውል የሚመነጭ ቢሆንም ከህግ ወይም ከፍርድ ሊመነጭም ይችላል፡፡

## 5.1 ዋስትና የሚደረግበት ሁኔታ

የዋስትና ግዴታ አሁን ያለን አንድ የተረጋገጠ ዕዳ ወይም ወደፊት በዋናው ባለዕ ላይ ሊመጣ የሚችልን ኃላፊነት ለመቀበል ሊደረግ ይችላል፡፡ በኋለኛው ምክንያት የሚያደረገው የዋስትና ግዴታ በዋናው ባለዕዳ ላይ ዕዳ ከሌለ በቀር ዋሱ ዋስትናውን ሊያስቀር ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ አንድ ግዴታ ከመጠየቁ በፊት የሚመሰረት ቢሆንም ዕዳው በሚጠይቅበት ጊዜ *(when the debtor is at default)* ወይም ዕዳው መጠየቅ ከጀመረ በኋላም ቢሆን ሊደረግ ይችላል፡፡ በየትኛውም መንገድ ቢሆን ግን ካለ ወይም ከሚመጣ ዕዳ ጋር የተቆራኘ ነው *(it is accessory in nature)* ፡፡ ዕዳ ሳይኖር የዋስትና ግዴታ አይኖርም፡፡ ዋናው ግዴታ የማይፀና ሲሆን የዋስትና ውሉም እንዲሁ አይፀናም፡፡ የባለዕዳውን ችሎታ አለመኖር ወይም የፈቃድ ጉድለት እያወቀ ዋስ ከሆነ ግን ዋናው ግዴታ የሚፀና ባይሆንም እንኳ ዋሱ ለባለገንዘቡ ግዴታ የገባበትን ገንዘብ መክፈል ይጠበቅበታል፡፡

የዋስትናውን ልክ በተመለከተ ዋስትና ከዋናው ግዴታ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ ዋናው ባለዕዳ የማይጠየቅበትን ዋሱ አይጠየቅበትም፡፡ እንዲህ ያለ ስምምነት ተደርጎ ከሆነም በዋናው ዕዳ ልክ ይቀነሳል፡፡

## 5.2 የዋስትና ግዴታ ሊከተለው የሚገባ የአፃፃፍ ሥርዓት

የዋስትና ግዴታ ከፍ ያለ ኃላፊነትን የሚያስከትል በመሆኑ ዋስ የሚሆን ሰው የሚገባበት ግዴታ የሚያስከትልበትን ኃላፊነት እንዲረዳው ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም ዋሱ በጥድፊያ ግዴታ ውስጥ ሳይገባ የአፍታ ጊዜ አግኝቶ እንዲያስብበት ዕድል ለመስጠት ውሉ በጽሁፍ እንዲሆን ህግ ያዛል (1725 cum 1922) ፡፡ ግዴታ የሚገባበት የገንዘብ መጠንም መታወቅ አለበት፡፡ ይህ ያልተሟለ እንደሆነ ውሉ ፈራሽ ይሆናል፡፡

## 5.3 የዋስትና ግዴታዎች ዓይነት

ከኃላፊነቱ ቆይታ አንፃር ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ (continuous guarantee) ፣ ከሚያስከትለው ኃላፊነት አንፃር ተራ እና የአንድነት ዋስትና፣ ለዕዳው ኃላፊ ከሚሆነው ክፍል

(subject) አንፃር የሰው ዋስትና እና የንብረት ዋስትና በማለት ልንከፍለው እንችላለን፡፡ በየመልካቸው እንደሚከተለው ልናያቸው እንሞክራለን፡፡

### 5.3.1 ለተወሰነ ጊዜ እና ለልተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የዋስትና ግዴታ

ዋስትና ልኩ እና የሚከፈልበት ጊዜ ለታወቀ አንድ ግዴታ አፈፃፀም ሊመሰረት ይችላል፡፡ የዛሬ ዓመት ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም በቀለ መክፈል ላለበት የብር 42,000 ዕዳ አከፋፈል ዋስ እንደመሆን ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል በዋስትና ግዴታ ከተገባበት የገንዘብ መጠን በቀር በዋናው ግዴታ የሚፈለገው የገንዘብ ልክ ለማይታወቅ፣ የዋስትና ኃላፊነቱ ጊዜም ላልተወሰነ ጉዳይ የዋስትና ግዴታ ሊመሠረት ይችላል፡፡ continuous guarantee ይባላል፡፡

በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር በዘበኝነት የተቀጠረ ሰው በሥራው ላይ ባለበት ጊዜ ሊጠፋበት/ሊጠይቅበት ለሚችል ዕዳ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) ድረስ ዋስ እንደመሆን ማለት ነው፡፡ ዕዳው አልመጣም፤ የሚመጣበት ሁኔታ ግን ሊኖር ይችላል፡፡ የዋስትናው ኃላፊነት ቆይታም በጊዜ የተገደበ አይደለም፡፡ እንዲህ ያለውን የዋስትና ግዴታ በተመለከተ የዋናው ባለዕዳ ተጠያቂነት ካልደረሰ በቀር ዋሱ ዋስትናውን እንዲወርድለት ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ***"ተጠያቂነቱ ካልደረሰ"*** ማለት ዋሱ ዋስትናው እንዲቀርለት በሚጠይቅበት ጊዜ ዋናውን ባለዕዳ ተጠያቂ የሚያደርግ ነገር ያልተገኘ እንዲሁ ማለት ነው፡፡ መስሪያ ቤቱ ይህንኑ አጠርቶ ነፃ ማድረግ ይገባዋል፡፡ ሠራተኛው ምትክ ዋስ ማቅረብ ካለበት ያንኑ መጠየቅ የመስሪያ ቤቱ ድርሻ ነው፡፡ ይህ ግን የዋሱን የዋስትና ግዴታ ከማውረድ መብቱ ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡ ምትክ ዋስ ቢገኝም ባይገኝም ዋሱ ግዴታው እንዲወርድለት ከጠየቀበት ጊዜ ጀምሮ ቀሪ ሊደረግለት ይገባል፡፡

### 5.3.2 ተራ እና የአንድነት ዋስትና

#### *ሀ. ተራ የዋስትና ግዴታ*

ይህ ዓይነቱ የዋስትና ግዴታ ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ሳይፈፅም ሲቀር ብቻ የሚመጣ ነው፡፡ ባለገንዘቡ የዋናውን ባለዕዳ ግዴታ ዋሱ እንዲፈፅምለት የሚጠይቀው ይኸው ባለዕዳ ግዴታውን ለመፈጸም የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ባለዕዳ መክሰሩ በፍርድ ካልተረጋገጠ በቀር ዋሱ እንደተከሰሰ ባለገንዘቡን ከዋናው ባለዕዳ ጋር ተከራከር የማለት መብት ይኖረዋል፡፡ ካለነሳው ግን ባለገንዘቡ ከባለዕዳው ጋር ለመከራከር ሳይገደድ በዋሱ ሀብት ላይ ዕዳውን ሊያስፈጽም ይችላል፡፡ መከራከሪያውን አንስቶ ቢሆን እንኳ የባለዕዳውን ንብረቶች መምራትና ለዚሁም ክርክር የሚያስፈልገውን በቂ ወጪ ለባለገንዘቡ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን አለማድረግ ከባለዕዳው ጋር ተከራከር የማለት መብቱን የሚያሳጣው ይሆናል፡፡

*ለ. የአንድነት ዋስትና*

የአንድነት ዋስትና የሚመሰረተው ዋሱ ከባለዕዳው ጋር በጋራ ተጠያቂ መሆኑን ወይም ይህን በመሰለ በማናቸውም ሌላ መንገድ ሀሳቡን በመግለጽ ግዴታ የገባ እንደሆነ ነው፡፡ ከዋናው ባለዕዳ ጋር ተከራከር የማለት መብት አይኖረውም፡፡ ባለገንዘቡም ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድነት ምናልባትም ከዋናው ባለዕዳ በፊት ሁሉ ክስ ሊቀርብበት የሚችል ሰው ነው፡፡

**5.4 የዋስ መብቶች**

***ሀ. የመዳረግ መብት -***

ዋሱ ስለዋናው ባለዕዳ ሆኖ የከፈለውን ተገቢ የሆኑ ክፍያዎች ሁሉ በባለገንዘቡ መብት ተዳረጊ ሆኖ ባለዕዳውን ሊጠይቀው ይችላል፡፡


***ለ. ከዋናው ባለዕዳ ጋር ተከራከር የማለት መብት -***

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይህ የተራ ዋስትና ግዴታ ያለበት ሰው የሚኖረው መብት ነው፡፡ እንደተከሰሰ ወዲውኑ ከዋናው ባለዕዳ ጋር ተከራከር በማለት ባለገንዘቡን የመከራከር መብት ይኖረዋል፡፡

***ሐ. ባለዕዳው ሊያነሳቸው የሚችላውን መቃወሚያዎች ማንሳት-***

ከግዴታው ዓይነት የተነሳ እንዲቀሩ ካልሆነ በቀር (ለምሳሌ ውሉ የተፈፀመው በስህተት መሆኑን ወይም ባለዕዳው ለአቅም አዳም ያልደረሰ መሆኑን እያወቀ የገባበት ግዴታ) ባለዕዳው ሊነሳቸው የሚችላቸውን መቃወሚያዎች እያነሳ ሊከራከርባቸው ይቻላል፡፡

# የዋስትና ዓይነቶች




## የሞርጌጅ የሚመሰረትበት መንገድ

1. በህግ
2. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ
3. በውል

## ሀ. በህግ (3042 እና 3043)

1. ህጉ ራሱ የሚሰጠው ዋስትና ነው፣
2. የዋስትና ሰጪ ስምምነት አስፈላጊ አይደለም፣
3. ለሁለት አይነት ሰዎች ዋስትና ይሰጣል፣

1. የማይንቀሳሰስ ንብረት ለሽጠ ለሽያጩ ዋጋ አከፋፈል እና በሽያጩ ውስጥ ለተመለከቱት ሌሎች ግዴታዎች፣
2. የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ተካፋይ ለሆነ ከክፍያው ውስጥ ለሚጎድልበት እና በክፍያው ያገኘው ሃብት እንዲለቅ ለተወሰነበት

## ለ. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ (3049)

- ዳኞች ወይም ሽማግሌዎች ለሰጡት ብይን ወይም ትዕዛዝ ተፈጻሚነት ዋስትና እንዲሆን የሚሰጥ፣
- በዳኞች ወይም በሽማግሌዎች ትዕዛዝ ብቻ የሚመሰረት፣
- የዋስትና የሚሰጠው ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት ሊሆን ይችላል፡፡
- አላማው እረታለሁ ብሎ የሚያስብ ተከራካሪ ንብረቱን ቀድሞ በማሸሽ አፈጻጸሙን እንዲያስናክል ነው፣
- ዋስትናው የሚመሰረተው ንብረቱ ዋስትና የሆለነትን የገዘብ መጠን እና የንብረቱን አይነት ለይቶ በመግለፅ እና ትዕዛዙን በማስመዝገብ ነው፡፡
- ትዕዛዙ በንብረቱ ሌላ ገደብ መጣል የለበትም፣
- በፍርድ ቤቶች ለውሳኔ ማስፈጸሚያ እንዲሆን ንብረቶች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 154 መሰረት የሚያግዱ ሲሆን ይህ ሥነ ሥርዓት ህግ አላማ የተለየ ነው፡፡ ውሳኔ ለማስፈጸም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚሰጥ ዋስትና ሲመሰረት ንብረቱ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ወይም በሌላ እዳ እንዳይሰጥ አስፈላጊ አይደለም፣

## ሐ. በውል የሚቋቋም መያዣ (3041)

- ተበዳሪው ራሱ ንብረቱን በማስያዝ
- ሌላ ሰው ለተደደሪው ንብረቱን በማስያዝ ይመሰረታል

# ለሚጸና ሞርጌጅ አስፈላጊ ሁኔታዎች

## *1. የሚቋቋምበት ሰነድ*

- በውል የሚቋቋም መያዣ በፁሁፍ መሆን አለበት (3045(1)) ፣ (1723)
- አዋዋይ ወይም ዳኛ ፊት መደረግ አለበት (1723)
    - ይህ ፎርማሊቲ ማስፈለጉ በፍ/ህ/ቁ 1723 ተመልክቷል፡፡
    - በውል የሚቋቋም ሞርጌጅ ውል እንደመሆኑ የጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎች የሞርጌጅን ህግ አስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚ ሊሆኑ ይችላሉ
    - አዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት መደረጉ የራሱ አላማ አለው፣
- መያዣ የተሰጠበት የገንዘብ ልክ እና የንብረቱ አይነት በግልፅ መግለፅ ያስፈልጋል (3045(2) ፣ 3048)

## 2. ምዝገባ

- የመያዣ መብቱ በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ ውስጥ ካልተፃፈ በቀር ማንኛውም አይነት ውጤት አያስገኝም 3052
- በየትኛውም ዓይነት መንገድ የተመሰረተ ሞርጌጅ ሊመዘገብ ይገባል፣
- ምዝገባው በንብረቱ ላይ ያለውን ግዴታ ለሶስተኛ ወገን ከማሳወቅ ባለፈ በተዋዋዩቹ መሃከል ውጤት አለው፣
- ከዚህ በተጨማሪ የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን አስፈላጊ ነው፣
- ምዝገባው ውጤት የሚኖረው ንብረቱ የተላለፈለት ሰው መብቱን ከማስመዝገቡ በፊት ወይም ንብረቱ ከመያዙና ከመመዝገቡ በፊት ከተከናወነ ነው (3057 (1)) እና (2))

## 3. መያዣ ለመስጠት የሚያስፈልግ ችሎታ (3049)

- ለራሱ እዳ ንብረቱን በመያዣ ለመስጠት ንብረቱን በገንዘብ ለሌላ 3ኛ ሰው ማስተላለፍ መብት ያለው ነው (3049(2))
- ለሌላ ሰው እዳ ንብረቱን በመያዣ መስጠት የሚችለው ደግሞ ንብረቱን ያለወጋ ማስተላለፍ መብት ያለው ነው (3049(3))

- ችሎታ የሌለው ሰው የሰጠው መያዣ ዋጋ የሌለው ሲሆን መብቱን ወይም ችሎታውን ኋላ አግኝቷ እንኳን ሆን ቀድሞ የሰጠው መያዣ ዋጋ የለውም (3050(2)(3))
- በሚመለከተው አስተዳደር ክፍል የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ከተሰጠው ሰው ጋር የተመሰረተ መያዣ ውል ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ማስረጃ ፍርስ ሆኖ ቢሰረዝ እንኳን ህጋዊ ውጤት አለው (3051(2))

## ***ሞርጌጅ የሚመለከታቸው ንብረቶች***

### 1. የማይንቀሳቀስ ንብረት

- ❖ ሞርጌጅ የሚመሰረተው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ብቻ ነው (3047(1))
- ❖ ህጉ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች እንደማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣ ሊሰጡ እንደሚችሉ ሊደነገግ ይችላል፡፡(3047(2)) ለምሳሌ የንግድ መደብር
- ❖ የማንቀሳቀስ ንብረት የሚባሉት መሬትና ህንፃ ቢሆኑም አሁን ባለው ሁኔታ በመያዣ መስጠት የሚቻለው ህንፃን ብቻ ነው
- ❖ የከተማን ቦታ የማከራየት መብት በመያዣ ሊሰጥ ይችላል (አዋጅ ቁጥር 272/94አንቀፅ 13)
- ❖ ወደፊት የሚሰሩ ህንፃዎች በመያዣ መስጠት አይቻልም (3050(3))

### *2. የንብረቱ ሙሉ ክፍል /intrinsic elements እና በተጨማሪ/accessories (3064)*

- ❖ ከንብረቱ ላይ ንብረቱ ሳይጠፋ እና አጉል ሳይሆን ለመለየት የማይቻል የንብረቱ ሙሉ ክፍል የመያዣው አካል ነው(1132)
- ❖ አንድን ነገር በሚጠቀምበት ሰው ሀሳብ ይህ ነገር ለሚገለገልበት ጉዳይ በነዋሪ ዓይነት ከዚሁ ጋር ተያያዞ የሚኝ ነገር ተጨማሪ ነገር ወይም ደባል ነገር ይባላል(1136)፡፡ ይህም የመያዣው አካል ነው
- ❖ እነዚህ ንብረቶች ከዋናው ንብረት ላይ ከተለዩ ግን የሚንቀሳቀስ ንብረት ሆነው ስለሚቆጠሩ የመያዣው አካል መሆናቸው ይቀራል(3065(1)፣1133፣1137)
- ❖ ከመያዣው ላይ በመነሳታቸው የንብረቱ ዋጋ ከቀነሰ ባለገንዘቡ አግባብነት ባላቸው ሞርጌጅ ህግ ድንጋጌዎች ሊሰራባቸው ይችላል(3065(2))

### 3. በንብረቱ ላይ የሚደረጉ አዲስ ወይም ተጨማሪ ስራዎች (3066)

- ❖ በህንፃው ላይ ተስፋፍተው የተሰሩ ወይም በንብረቱ ላይ የተደረጉ የማሻሻያ ስራዎች የመያዣው አካል ናቸው

### 4. ኪራይ፣ለንብረቱ የተከፈለ ኢንሹራንስ፣ንብረቱ ሲለቀቅ የሚከፈለው ካሳ ሁሉ የመያዣው አካል ናቸው(3068)

## ***ምርጌጁ መድን የሆነላቸው እዳዎች***

1. ዋናው እዳ
2. ወለድ
   - ❖ ተዋዋይ ወገኖቹ በውላቸው ላይ የተስማሙበት የወለድ መጠን(3077(1))
   - ❖ መያዣው መድን የሚሆንለት ወለድ ግን የ2 ዓመት ብቻ ነው(3077(2))
   - ❖ ከ2 ዓመት በላይ ለሆነው ወለድ መያዣው የቀዳሚነት መብት አይሰጠውም። ቀዳሚነት መብት እንዲሰጠውም መስማማት አይችሉም(3077(3))
   - ❖ ተዋዋዮች የተስማሙበት ወለድ ባይኖር እንኳን ንብረቱ ተይዞ እስከሚሸጥ ድረስ ህጉ የሚያስበው ወለድ

3. ባለገንዘቡ የከፈለው የኢንሹራንስ ክፍያ(3078)
4. ባለእዳው ዋናውን ግዴታ ባለመወጣቱ ባለገንዘቡ ንብረቱን ተከታትሎ ለማስያዝ እና ንብረቱን ለማሸጥ የወጣ ወጪ

## ***የምርጌጅ ውጤቶች***

### 1. ***በገንዘብ ጠያቂዎች ላይ ያለው ውጤት***

#### ***የቅድሚያ መብት(3059(1))***

- ❖ የቅድሚያ መብት የሚነሳው ብዙ ገንዘብ ጠያቂዎች ሲኖሩ እና የሽያጩ ገንዘብ የሁሉንም እዳ ሳይሸፍን ሲቀር ነው

- የማይንቀሳቀስ ንብረት ከአንድ በላይ ለሆነ እዳ በመያዣነት ሊሰጥ ይችላል፡፡ በመሆኑም መያዣ መብት ያላቸው ብዙ ገንዘብ ጠያቂዎች ሊኖር ይችላሉ(3088(1))
- የመያዣ መብት የሌላቸውም ገንዘብ ጠያቂዎች ሊኖሩ ይችላሉ
- የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ማንኛውም ገንዘብ ጠያቂ በመያዣ የተሰጠውን ንብረት እንዲያዝ እና እንዲሸጥ ለመጠየቅ ይችላል(3059)
- ቅድሚያ ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብቱ ከሽያጩ ላይ ከሌሎች ባለገንዘቦች ገንዘቡን የማግኘት ነው(3059)
- በመያዣ የተያዘውን ንብረት ላይ የተሰራ አዲስ እና የማሻሻያ ስራ የሰሩ፣ለስራው እቃ እየሸጡ፣አትክልትና ዘር የሰብል ፍሬ ቀረቡ ሰዎች ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው(3067(1))

## <u>ንብረቱን የመከተል መብት (3059(2))</u>

- ንብረቱን የመተል መብት የሚሰራበት ባለእዳው ግዴታውን መወጣት ካልቻለ እና ንብረቱ ለሌላ ሰው ተላልፎ ከሆነ ነው
- ንብረቱንም ንብረቱ ከተላለፈለት ሰው እጅ እንዲያዝ ሊጠይቅ የሚችለው የመያዣ መብቱን የንብረቱ መሸጥ ፅሁፍ በመዝገብ ከመፃፉ በፊት ከተመዘገበ ነው(3085)
- ሞርጌጅ የማይከፋፈል በመሆኑ ባለእዳው ከፊል ግዴታው ተወጥቶ እንኳን ቢሆን ለቀሪው እዳ ንብረቱ በሙሉ ተይዞ ሊሸጥ ይችላል(3077)
- ንብረቱ ለመሸጥ ሲያዝ የንብረቱ መያዝ የሚያስከትላቸው ውጤቶች አሉ
    - የወለድ ስሌት(3077)
    - ኪራይ አሰባሰብ ላይ (3068)
    - ንብረቱ ላይ የሚደርስ ጉዳት(3107)
        - በአስያዡ ወይም ንብረቱ በተላለፈለት 3ኛ ወገን ድርጊት ወይም ቸልተኝነት የሚደርስ ጉዳት
        - የንብረቱ መጥፋት ወይም መበላሸት ንብረቱን የገዛው 3ኛ ወገን ኃላፊ የሚሆነው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኛነት ድርጊትን የፈፀመው ከሆነና

ይኸውም የተከናወነው ንብረቱ በፍርድ የማስያዝ ስነ-ስርዓት ከተጀመረና ማስታወቂያ ከተላከ በኂላ ከሆነ ነው(3092)

**<u>የተራ ባለገንዘብ መብት (3059(3))</u>**

❖ ንብረቱ ተሸጦ ሽያጩ ገንዘብ እዳውን ያልሸፈነ ከሆነ ባለገንዘቡ የተራ ባለገንዘብ መብት አለው፡፡

## 2. ንብረቱን ባስያዘው ሰው ላይ ያለው ውጤት

ንብረቱን የማስተላለፍ፣ በድጋሚ በመያዣ መስጠት፣ ገቢና ጥቅሙን መሰባሰብ (3059(2))፣ 3089፣ 3093)

- ግዴታው ከንብረቱ ዋጋ አይበልጥም (3105)
- ሞርጌጅ የሚፀናው ለ10 አመት ብቻ ነው (3058፣ 1632)
- ለንብርቱ ዋጋ መጓደል ሃላፊ ነው (3107፣3073፣3074)
- በንብረቱ ላይ የተሰራ አዲስ ስራ እና ማሻሻያ የመያዣው አካል ነው (3066)
- እዳው ካልተከፈለ ንብረቱ ተይዞ ይሸጣል
- የንብረቱን ዋጋ ከፍሎ መያዣውን የማስለቀቅ (Redemption) መብት የለውም፣

## 3. በ3ኛ ወገኖች ላይ ያለው ውጤት

## ዋስትና በሌላቸው ባለገንዘቦች ላይ ያለው ውጤት

❖ እዳ መክፈያቸው ከደረሰ ንብረቱ ተያይዞ እንዲሸጥ ሊጠይቁ ይችላሉ (3059፣ 1988)

## ዋስትና ባላቸው ባለገንዘቦች ያለው ውጤት

❖ ብዙ መያዛ ያላቸው ባለገንዘቦች ሊኖሩ ይችላሉ

- የቀዳሚነት ቅደም ተከተላቸው መያዣቸውን ባስመዘገቡበት ቀን ይወስናል (3081)
- በአንድ ቀን ያስመዘገቡ ባለገንዘቦች መብት በእኩል ደረጃ ይታያል (3082)
- የቀደሚነት መብት ተራ በክፍያ ሊወስድ ይችላል (Subrogation (3083))

## ንብረቱ በተላለፈለት ሰው ላይ ያለው ውጤት

### ሀ. የስራቸው የማሻሻያ ስራዎች (3091)

- ለስራቸው አዲስ ስራዎች ወይም ማሻሻያዎች ዋጋ እንዲከፈለው ሊጠይቅ ይችላል፡፡
- ዋጋውን ሊጠይቅ የሚችለው የሽያጬን ፁሁፍ ካስመዘገበ በኂላ ለሰራው ስራ ብቻ ነው

### ለ) የንብረቱ መጥፋት ወይም መበላሸት

- ለንብረቱ መጥፋት እና መበላሸት መያዣ ገንዘብ ጠያቂዎች ኃላፊ አይሆንም
- ኃላፊነት የሚኖርበት ንብረቱ የጠፋው ወይም የተበላሸው የንብረቱ መያዝ ሥነ-ሥርዓት ከተጀመረ በኂላ በርሱ አድራጎት እና ቸልተኛነት ከሆነ ነው

### ሐ) መድን/ warranty (3094፣ 2882)

- በመያዣ የተሰጠውን ንብረት የገዛ ሰው ንብረቱን እንዲለቅ ቢደረግ ሻጩን መድን እንዲሆነው ሊያስገድደው/ ክስ ሊያቀርብበት ይችላል (3094)
- ይህ ክስ ሊወገድ የሚችለው በሽያጩ ውል ላይ ሻጩ መድን የማይሆን መሆኑን በግልፅ ተመልክቶ ከሆነ ብቻ ነው (3094(3))
- ንብረቱ ያለዋጋ የተላለፈለት ሰውም የመድንነት ክስ ሊያቀርብ ይችላል (3094(2))

### መ) መተካት/ subrogation(3095)

- በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የመያዣ መብት በነበረው ሰው በመተካት በመብቱ ሊሰራበት ይችላል
- ንብረቱ በገንዘብ ጠያቂው ምክንያት የተሸጠበት ሰው ዋናውን ባለእዳ ለባለገንዘቡ ሊከፍለው የሚገባውን ያህል እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት አለው

## ሠ) ፈቅዶ ገንዘብ በመክፈል ንበረቱን ማስቀረት/ voluntary discharge of debt (3097)

- ❖ ንብረቱ የተያዘበትን ሙሉ እዳ በመክፈል ንብረቱን ከመያዣው ነፃ ማድረግ ይችላል
- ❖ ክፍያው ያልደረሰውን እዳ ከፍሎ ንብረቱን ነፃ ማድረግ የሚቻለው የባለገንዘቡ ስምምነት ሲኖር ነው
- ❖ ንብረቱ በመያዣ ከተያዘ በኂላ ግን ስምምነቱ አስፈላጊ አይደለም

## ረ) ማስለቀቅ/ redemption (3090)

- ❖የንብረቱን ትክክለኛ ዋጋ በመክፈል ንብረቱን ማስለቀቅ ይቻላል
- ❖ንብረቱ መያዣ የሆነለትን እዳ በሙሉ መክፈል ሳያስፈልግ የንብረቱን ትክክለኛ ዋጋ ብቻ በመክፈል ንብረቱን ማስቀረት
- ❖ይህን ለማድረግ የሁሉም የመያዣ መብት ያላቸው ባለገንዘቦች ስምምነት ያስፈልጋል
- ❖የማስለቀቅ መብት ተጠቃሚ የሆነው እዳው በግል የማይመለከተው ሰው ብቻ ነው
- ❖ጥያቄው መቅረብ ያለበት የንብረቱ የመያዝ ትዕዛዝ ከመመዝገቡ በፊት ነው
- ❖የማስለቀቁ ጥያቄ ከቀረበ በኂላ ጠያቂው ለሁለት ወር በጥያቄው ይገደዳል
- ❖እስከ ሁለት ወር ባለገንዘቦቹ ተቃውሚቸውን ካላሳወቁ እንደተስማሙ ይቆጠራል
- ❖ካለተስማሙ ንበረቱ በሐራጅ ይሸጣል

## ሸ) እንደዋስ ስለመቆጠር/ assimilation to suretyship (3090)

- ❖ ገዢው ከባለገንዘቡ ጋር በሚኖረው ግንኙነት በጠቅላላ ውል ህግ ላይ ዋሱ ሊያነሳቸው የሚችላቸው መብቶች እንዲጠቀምባቸው መብት ተሰጥቶታል
- ❖ ባለገንዘቡ እዳውን ዋሱ እንዲከፍል ከማስገደዱ በፊት በዋናው ባለእዳ ሃብቶች ላይ እንዲከራከር ይፈቅድለታል
- ❖ ይህንኑ መብት መያዣ የተሰጠበትን ንብረት የገዛው ሰው እንዲገለገልበት ህጉ ፈቅዶለታል
- ❖ ንብረቱን አስይዞ ለሌላ ሰው ዋስ የሆነ ሰው መያዣ የተሰጠበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት እንደገዛ 3ኛ ወገን ይቆጠራል (3106)

# የንግድ መደብር ሞርጌጅ

የሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚመሰረት ሞርጌጅ ነው

በንግድ ሕጉ በተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር የሚተዳደረው በፍ/ሕጉ ውስጥ በሚገኙ ድንጋጌዎች ነው (ን/ሕ/ቁ 1)

## 1. የመያዣው አመሠራረት

- ከውል ወይም ከሕግ ይመሠረታል
- በፍርድ የሚቋቋም ለመሆኑ የንግድ ሕጉ አያመለክትም

## ከሕግ የሚመነጭ (172)

- የንግደ መደብሩን ለሸጡ
- በነጋዴው መክሰር በወል ገንዘብ ጠያቂዎች

## ለሻጮች የተሰጠው የሕግ መያዣ መብት

- በሸጡት የንግድ መደብር ላይ የመያዣ መብት አላቸው
- የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ይችላሉ

## የመያዣ አመዘጋገብ

- ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ምዝገባ አስፈላጊ ነው (ን/ሕ/ቁ 174፣178፣ 179)
- ምዝገባው በተወሰነ ቀን ውስጥ መደረግ አለበት (173፣ 177)

## መያዣው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

- መያዣው ፀንቶ የሚቆየው ለ5 ዓመት ብቻ ነው

## ለባንክ በመያዣ የተሰጡ ንብረቶች

- በተወሰኑ የፍትሐ ብሔር እና የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያ ተደርጓል
- የመጀመሪያውን ማሻሻያ ያደረገው አ/ቁ 65/89 ነው
- ይህ አዋጅ በፍ/ሕ/ቁ 2851 እና 3060 ላይ ማሻሻያ አድርጎባቸዋል
- ማሻሻያው የሚመለከተው ባንክ በመያዣ የተያዙ ንብረቶች አሻሻጥ ሥርዓትን ነው
- ባንክ በመያዣ የያዘውን ንብረት ወደ ፍ/ቤት መምጣት ሳያስፈልገው ራሱ እንዲሸጥ
- የሚያደርገ ስምምነት ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው ተደርጓል
- አ/ቁ 97/90 ከፍ ሲል የተጠቀሰውን አዋጅ ሽሮታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለባንክ በመያዣ የተሰጠ የንግድ መደብርን በተመለከተ አ/ቁ 98/98 በንግድ ሕጉ ላይ ማሻሻያ አድርጓል
- እነዚህ አዋጆች ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች ራሱ እንዲሸጥ የሚያደርገውን ስምምነት ህጋዊነት ይቀበላሉ
- አዋጆቹ ከመውጣታቸው በፊት እና በኋላ በመያዣ በተሰጡ ንብረቶች ላይ ልዩነት አድርገዋል
- አዋጆቹ ከመውጣታቸው በፊት ለባንክ በመያዣ የተሰጡ ንብረቶችን በተመለከተ ባንኩ የተዋዋዮቹ ስምምነት ሳያስፈልገው ንብረቶቹን ራሱ ለመሸጥ ህጉ መብት ሰጥቶታል
- አዋጆቹ ከወጡ በኋላ በመያዣ የተሰጡ ንብረቶችን በተመለከተ ራሱ ለመሸጥ ግን ስምምነት ያስፈልገዋል
- ባንኩ ንብረቶቹን ራሱ ለመሸጥ ስምምነት ካላደረገ የፍትሐብሔር ህጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ
- በአሻሻጥ ሥርዓቱ ላይ ከተደረገው ለውጥ በቀር የፍትሐብሔር ህጉ ሆነ የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አላቸው

## ሞርጌጅ ቀሪ የሚሆንባቸው ምክንያቶች (3110)

1. መያዣው የሚመለከተው የገንዘብ መጠየቂያ መብት ቀሪ ሲሆን
2. የመያዣ መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ የመያዣው ይቅርብኝ ብሎ ሲተው
3. ንብረቱ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡ ለባለገንዘቦቹ ሲከፈል

4. መያዣው እንዲለቀቅ ጥያቄ በቀረበበት ጊዜ የቀረበውን ገንዘብ ገንዘብ ጠያቂዎች ተቀብለው በባለመብቶቹ መካከል ገንዘቡን የተከፋፈሉ ከሆነ
5. ሞርጌጁ ከተመዘገበ 10 ዓመት ሲያልፈው
6. መያዣ የተሰጠበት ንብረት ሲወድም

## በዋስትና ጉዳዮች ለመወያየት የቀረቡ መልመጃዎች

1. ኃይሉ ኤጀርሳ ለአቶ ታደሰ ኃ/ሚካኤል ብር 9746 አድጓል፡፡ በውሉ ላይ በተገለፀው ቀን ገንዘቡን ባይመልሱ ብር 3000 መቀጫ ጨምረው ለመክፍል ተስማምቷዋል፡፡ ስለዕዳው አፈፃፀምም አቶ ፀጋው ወሌ ዋስ በመሆን ግዴታ ገብተዋል፡፡

   ብር 4500 ከተከፈለ በኃላ ቀሪ ገንዘብ በጊዜው ባለመክፈሉ አቶ ኃይሉ ቀሪው ብር 5246 ከመቀጮ ገንዘብ ጋር ተደምሮ ይከፈለኝ በማለት ጠየቁ፡፡

   ዋሱ እኔ የተዋልኩት ለዋናው ዕዳ አፈፃፀም እንጂ ለመቀጫው አይደለም፡፡ ስለሆነም በገደብ ገንዘቡ ላይ ልጠይቅ አይገባም ይላሉ፡፡

   ዋስ የሆነ ሰው እንዲህ ያለ መከራከሪያ ሊያነሳ ይችላል?
   አቶ ታደሰ (ዋሱ ባለዕዳ) መቀጫውን የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው? (በጊዜው አልከፈሉም የሚለውን ታሳቢ አድርገው ይውሰዱት)

2. አቶ ዮሐንስ በላይ በገንዘብ ሚኒስቴር በጡረታ አባል ማከፋፈያ ዋና ክፍል ተጠባባቂ ዋና ገንዘብ ያዥ ሆኖ ሲሠራ ከቆየ በኋላ ከሥራ ገበታው ተሰውሯል፡፡

   ከ1986 - መስከረም 21 ቀን 1988 ዓ.ም ድረስ የሠራበት ሂሳብ ሲመረመር 1557፣ 779.20 ጉድለት ታይቶበታል፡፡ ይኸው ገንዘብ ከወለድ ከኪሣራና ወጪ ጋር እንዲከፈለው በባለዕዳው ላይ ክስ ሲመሠረት እስከ ብር 50000 ድረስ ዋስ በመሆን ግዴታ የገቡትን አቶ መንገሻ አክሎ ግን አብሮ ከሷል፡፡

ዋሱ በ1986፣ 87፣ 88 በተደጋሚ ጉድለት ሲከሠት ሳያሳውቀኝ ወይም ተገቢውን ክትትል በጊዜው ማድረግ እየተገባው ከፍተኛ ጉድለት ከመጣ በኃላ ሊጠይቀኝ አይገባም፡፡ ንብረት እንዲሸሽም ምክንያት ሆኗል፡፡ በ 1928(2)፣ 1934(2)፣ 1935 እና በ 1947 መሠረት ልጠየቅበት አይገባም በማለት ይከራከራል፡፡

ፍርድ ቤቱ ዋሱ ግዴታ የገባበትን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል ተባለ፡፡ የዋሱን ክርክር እና የፍርድ ቤቱን ውሳኔ እንዴት ይመለከቱታል? ባለገንዘቡ የዋሱን ዕዳ የሚያከብድ ነገር እንዳይኖር ወይም ያለ በሆነ ጊዜ ይህንኑ ለዋሱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት?

3. አቶ ማሞ ጉበና ለአቶ ወርቅነህ በላቸው  አንድ ላንድሮቨር መኪና በብር 14000 ሸጠዋል፡፡ 10000 ተከፍሏል፡፡ ቀሪው ብር 4000 ስላለተከፈለ ከነመቀጫው ብር 5000 እንዲከፍሉ ሲስማሙ አቶ በቃሉ ባለእዳው ዕዳውን መክፈል ባይቻሉ ሊከፍሉ ተስማምተው በዋስትና ግዴታ ገቡ፡፡ አልተከፈለም፡፡ አቶ ወርቅነህ ከዋሳቸው አቶ በቃሉ ጋር ተከሰሱ፡፡

ዋሱ አቶ በቃሉ ለቀርባባቸው ክስ መልስ ሲሰጡ

- ተራ ዋስ ነኝ …ተራ ዋስ ደግሞ መካሰስ ያለበት ዋናው ባለዕዳ ክስ ቀርበበት ከተፈረመበት በኃላ መክፈል ሳይችል የቀረ እንዲ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሂደት ሳይጠናቀቅ የአንድነት ባለ ዕዳ እንደሆንኩ ሁሉ ባለእዕዳው ጋር መካሰስ የለብኝም በማለት ይከራከራሉ፡፡

ፍርድ ቤቱ ተራ ዋስ መካሰስ ያለበት ዋናው ባለዕዳ ዕዳውን ለመክፈል አቅም የሌለው እንደሆነ ብቻ ነው በማለት ከባለዕዳው ጋር ዋሱ በአንድነት መከሰሱን ነቅፎ ከክሱ አስናብቷቸዋል፡፡

ተራ ዋስ መከሰስ ያለበት መቼ ነው? በፍርድ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድነው?

4. አቶ ወልደገብርኤል ገ/ሚካኤል የገንዘብ ሚኒስቴር ሰራተኛ ሆኖ ሲቀጠር በሥራው ላይ እያለ ለሚያደርሰው ጉድለት እስከ ብር 30000 ድረስ ዋስ በመሆን አቶ አብዱራህማን ግዴታ ገብተዋል፡፡

ከበርካታ ዓመታት በኃላ አቶ ወልደገብርኤል ብር 1365፣ 45 ጉድለት ተገኘባቸው፡፡ ዋሱ ይህንኑ ገንዘብ ከባለዕዳው ጋር እንዲከፈሉ ተጠየቁ፡፡

ዋሱ ጉድለቱ ከመድረሱ በፊት ዋስትናዬ እንዲወርድልኝ ለአሠሪው መስሪያ ቤት ማስታወቂያ የሰጠሁ ስለሆነ ግዴታዬ ቀሪ ሆኗል፡፡ መጠየቅ አይገባኝም ይላሉ፡፡

ፍርድ ቤቱም ዋስትና ውል ነው፡፡ ውል ቀሪ የሚሆነው ደግሞ በህግ አግባብ ነው፡፡ በፍ.ብ.ህ.ቁ. 1806 እና 1807 የተገለፁት ሁኔታዎች ሳይሟሉ ግዴታዬ ቀርቷል ማለት አይቻሉም በማለት የተጠየቀቁትን ገንዘብ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

ፍርዱ ተገቢ ነበር ብለው ያምናሉ?

5. በፍርድ የሚደረጉ የዋስትና ግዴታዎች ጥብቅ የሆነውን የአፃፃፍ ሥርዓት ከውል እንደሚመነጩ የዋስትና ግዴታዎች መከተል አለበት? ለምሳሌ ለአንድ የፍርድ ቦለዕዳ ዋስ የሆነ ሰው በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመዋስ እንደሚፈልግ በዝርዝር ተነግሮት ይኸው በዝርዝር ከተመዘገበ በኃላ ባለዕዳው ዕዳውን ሳይከፍል ቢቀር ዋሱ በጽሁፍ አለመደገፉን መከራከሪያ ሊያደርገው ይችላል? በጽሁፍ ሆኖም ቢሆን እንኳ የገንዘቡ መጠን አልተገለፀም ወይም ሁለት ምስክሮች አልፈረሙለትም ብሎ ሊከራከር ይችላል?

6. ወ/ሮ ምንትዋብ ከአቶ መሐመድ ዓሊ ለተበደሩት ብር 145000 አቶ ብርሃኔ ሀጐስ ዋስ በመሆን ግዴታ ገብተዋል፡፡ ግዴታቸው ተራ ዋስትና ነው፡፡ ወ/ሮ ምንትዋብ በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ብድሩን አልከፈሉም፡፡ ከሁለት ዓመት በኃላ በዋናው ባለዕዳ ላይና በዋሱ ላይ አቶ መሐመድ ክስ አቀረቡ፡፡

ዋሱ ወለዱን ሊጠየቅበት አይገባም፡፡ መጠየቅ ካለብኝም ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባለው ወለድ እንጂ ከዚያ በፊት ለነበረው ሲሆን አይገባም በማለት ይከራከራሉ፡፡ እርስዎ በዳኝነት ጉዳዩ ቢቀርብልዎ ክርክሩን እንዴት ይፈቱታል፡፡